# የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ደንብ፡ መመሪያና ማብራሪያ፡፡

## መቅድም፡፡

በቀደሙት ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከትውልድ ወደትውልድ፡ በትውፊት እየተላለፈና በልማድ እየተሠራበት የኖረው ይህ ሥርዓት፡ ለዘመናችን አሠራር ያመች ዘንድ፡ ጊዜውን ጠብቆ፡ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ቀንና ዓመተ ምሕረት፡ በሕጋዊ መልክ፡ በጽሑፍ ተዘጋጅቶና ታትሞ፡ በቃለ ዓዋዲ ሊወጣ ቻለ፡፡

ይህም፡ ያለምክንያት አይደለም፤ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት ጸንቶ፡ በዘለዓለማዊነት እንዲቀጥል ባደረገው፡ የምሕረት ቃል ኪዳኑ ምክንያት፡ በኖኅ ዘመን የደረሰውን ከመሰለው ጥፋትና ለዓለሙ ፍጻሜም፡ እንደ"ምጥ ጣር መጀመሪያ" ከሚቆጠረው መከራ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ከነሥርዓተ መንግሥታቸው ሊታደግ መኾኑ፡ እስካኹን በኾነውና አኹንም እየቀጠለ በኼደው የዘመናችን ትንግርት፡ እነሆ፡ በግልጽ ይታያል፡፡

በዚህ የትድግናው ተግባር ውስጥ፡ ከሌሎቹ መካከል፡ እኔም፡ ትሑት አገልጋዩ፡ በግንባር ቀደምትነት ተሳታፊ እንድኾን ማድረጉን፡ ካለፉት ውይይቶቻችንና ከመጻሕፍቴ ምንባብ እንደተረዳችሁ አውቃለሁ፤ አዎን! በሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት፡ በዚያን ዘመን፡ በሹመት በተቀበልሁት የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪጅነት ኃላፊነቴ፡ የደንቡን ረቂቅ፡ ከመምሪያውና ከማብራሪያው ጋር አዘጋጅቼ፡ ለደንብ አውጪው፡ የቤተ ክህነት ጉባኤ ካቀረብሁ በኋላ፡ ጸድቆ ለመታወጅ፥ በተግባርም ላይ ውሎ፡ የታቀደለትን መልካም ፍሬ ለማበርከት በቅቷል፡፡

የመለኮታዊው መንግሥት፡ የለሰለሰ እርሻ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊ ልቦና ላይ እንዲዘራ፡ ከእርሻው ባለቤት የተሰጠው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያዊነት፡ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ዘር፡ ለመልካም ፍሬያማነት ሊበቃ የቻለው፡ እንዲሁ፡ በቀላል መሥዋዕትነት አልነበረም፡፡ በመጀመሪያ፡ ለዚህ አገልግሎት የሚረዱ ባለሙያዎች ካህናትን፡ ከመላዎቹ የኢትዮጵያ ወረዳዎች መልምለን፡ ለስድስት ወራት አሠለጠንናቸው፤ ከዚህ በኋላ፡ ግዳጃቸውን እንዲፈጽሙ፡ አስቀድመን፡ እነርሱኑ፡ ወደየወረዳቸው መልሰን መደብናቸው፡፡

እንዲሁም፡ ለአጠቃላዩ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አድማጭ፡ እኔው ራሴ፡ በየዕለቱ ምሽት፡ ለሠላሳ ደቂቃዎች ያህል፡ በኢትዮጵያ ነፋስ ድምፅ፡ በቃሌ በማስረዳት፥ ከዚህም በላይ፡ ሥራው የሚመለከታቸውን፡ ባልደረቦቼን ይዤ፡ በየሳምንቱ የእሑድ ሰንበት፡ በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት፥ በአዘቦቱ የሥራ ቀናት ደግሞ፡ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ዋና ከተሞች፡ በመዘዋወር፡ ከባድ ጥረት፥ ትጋትና ትግል ታክሎበት እንደነበረ፡ በቅርብ የማስታውሰው እውነታ መኾኑን፡ እናንተም ልታውቁት ያስፈልጋችኋል፡፡

አኹንም፡ ከዚሁ፡ ከሰበካው ጉባኤ ደንብ ጋር አያይዤ አዘጋጅቼው የነበረውን፡ የደንቡን ማብራሪያና በተግባር ላይ የዋለበትን መመሪያ፡ ከመግቢያው በመነሣት፡ እንደሚከተለው አቅርቤላችኋለሁ፡-

# መግቢያ።

## የካህናትና የምእመናን ጉባኤ የኾነችው፡
## የ"ቤተ ክርስቲያን" ቤተ ሕዝብነት።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች የኾኑ ኢትዮጵያውያን ካህናትና ምእመናን፡ እያንዳንዳቸው፡ ስለቤተ ክርስቲያናቸው አቋምና አስተዳደር፥ እነርሱም፡ ካህኑ፡ በካህንነቱ፥ ምእመኑም፡ በምእመንነቱ፡ ያለባቸው ኃላፊነትና ግዴታ፡ ምን እንደኾነ፡ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ቤተ ክርስቲያናችን፡ የተቋቋመችባቸውን የተቀደሱ ዓላማዎች፡ ከግብ ለማድረስና ከኾነ ጀምሮ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ለአገራችንና ለሕዝቡ የፈጸመችውን በጎ ሥራ ኹሉ፡ አኹንም፥ ወደፊትም፡ ጊዜው በሚጠይቀው መልክ፡ በበለጠ አሻሽላና አስፋፍታ ለማበርከት የምትችለው፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የኾነው፡ ካህኑም፥ ምእመኑም፡ ኃላፊነቱንና ግዴታውን አውቆ፡ ተግባሩን፡ በትክክል ሊፈጽም ሲችል በመኾኑ፡ ከዚህ የሚከተለው ማብራሪያ፥ መምሪያም ተሰጥቷልና፡ ካህናትና ምእመናን፡ ይህንኑ፡ በጥንቃቄ ተከታትለው መፈጸም ያስፈልጋቸዋል።

"ካህን" የሚባለው የቤተ ክርስቲያን አባል፡ በቅዱስ ቍርባን በታተመ፡ ሕጋዊ ጋብቻ፥ ብሕትውና፥ ወይም፡ ምንኵስና ተወስኖ፡ ቤተ ክርስቲያንን፡ በቅስና፥ በዲቁና፥ በመዘምርነት (በድብትርና)፥ በአስተማሪነት፥ በሰባኪነት፥ ወይም፡ በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ተመድቦ፡ በቤተ ክህነትና በሌሎች የቤተ ክህነት ድርጅቶች ውስጥ የሚሠራ መንፈሳዊ አገልጋይ ነው።

"ምእመን" የሚባለው የቤተ ክርስቲያን አባል፡ "ወንድ"፥ "ሴት" ሳይባል፡ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ርትዕት በኾነችው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ የክርስትና ሃይማኖት፡ ሥርዓተ ጥምቀት ተፈጽሞለት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ጸጋ የተቀበለና በዘወትር ንስሓው፡ ቅዱስ ቍርባንን እየተቀበለ የሚኖር፡ ማናቸውም ሰው ነው።

ቤተ ክርስቲያን፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ተያይዞ የመጣውን አቋሟንና የአስተዳደር አመራርዋን በመከተል፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት፡ ግድግዳና ጣራ ኾነው፡ ማኅበራዊ ቤት ያደረጓት ካህናትና ምእመናን፡ ይህንኑ፡ ሲያያዝ የመጣውን፡ ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን፡ ዛሬ፡ ዘመኑ በሚፈቅደው መልክ አደራጅተው እንዲሠሩ ማድረግ፡ አስፈላጊ መኾኑን በመረዳት፡ ከዚህ በታች በተጠቀሱት፡ ለቤተ ክርስቲያን በተሰጡት ሕጎች መሠረት፡ በቤተ ክርስቲያን ተግባር፥ አስተዳደርና ሀብት ውስጥ፡ ሙሉ ተካፋዮች እንዲኾኑ፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ፡ በሕጋዊ አዋጅ ተሰጥቷል።

ገበሬ፡ ለእርሻው፡ መሬት፥ ዘርና ማረሻ ካገኘ፡ ያርሳል፤ ነጋዴ፡ ለንግዱ፡ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ካገኘ፡ ይነግዳል፤ ወታደር፡ ለተሰለፈበት ዓላማ፡ በቂ ትጥቅ ካገኘ፡ ግዳጁን ይፈጽማል፤ ሌላውም ኹሉ፡ እንዲሁ ነው። እያንዳንዱ ካህን፥ እያንዳንዱ ምእመን፡ ስለቤተ ክርስቲያን፥ ስለሃይማኖቱ፡ የሚሠራበትን፡ ይህን መብትና ሥልጣን ካገኘ፡ በተሰጠው ፍቱን መሣሪያ፡ የሚገባውን መሥራት ይኖርበታል፤ ከአኹን በኋላ፡ እያንዳንዱ ካህን፥ እያንዳንዱ ምእመን፡ በተሰጠው መክሊት ሠርቶ፡ የሚጠበቅበትን ፍሬ ላለማበርከት፡ አንዳችም ምክንያት መፍጠር አይችልም።

እንግዴህ፡ እንደባዕድ ከውጭ ኾኖ፡ መንቀፍና ማማት የለበትም፤ በያለበት፥ በየሚኖርበት ሰበካ ውስጥ፡ ኹሉም፡ ወደየሰበካው ቤተ ክርስቲያን እየቀረበና እየተመዘገበ፡ በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር፥ ሥራና ሀብት ውስጥ፡ ተካፋይ መኾን ይኖርበታል።

እያንዳንዱ ካህን፥ እያንዳንዱም ምእመን፡ ይህን መብቱንና ተግባሩን አውቆ ቢሠራበት፥ ወይም፡ ባይሠራበት፡ ጌታችን፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሥራች ቃሉ በተናገረው መሠረት፡ በምድር፡ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፥ ኋላም፡ በሰማያዊው ጉባኤ ፊት ተጠይቆ፡ የሥራውን ዋጋ የሚቀበልበት ይኾናል።

በዚህ፡ በማቴዎስ ምዕራፍ ፳፭፥ ቊጥሮች ፲፬-፴ በተነገረው ጥቅስ ውስጥ የተመለከተው፡ ይህ ፍርድ የሚሰሰጠው፡ እያንዳንዱ ካህን፥ ወይም፡ እያንዳንዱ ምእመን፡ ባለው፡ የኀላፊነት መጠን መኾኑን፡ ምንጊዜም መዘንጋት የለብንም። የሰውን ሕግ፡ ጊዜ ይሽረዋል፤ ጊዜ ያሻሽለዋል። የእግዚአብሔርን ቃል ግን፡ ዘመናት አይወስኑትም፤ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር ስለኾነ፡ አቃልለን፥ ወይም፡ በዋዛ ልንመለከተው አይገባም።

ቤተ ክርስቲያን፡ እየጠነከረችና እየተስፋፋች እንድትኼድ የምንፈልገው ለምንድርነው? ከምንኖርበት ዓለም፡ በሞተ ሥጋ ከተለየን በኋላ፡ ስለሚጠብቀን የተስፋ ሕይወት ብለን ነውን? አይደለም፤ ለዚህ ብቻ ብለን አይደለም። ያ፡ በተስፋ የምንጠብቀው ሕይወት ስለሚገኝበት፡ ስለዚህ ዓለም ኑሮአችን መስተካከልና መደርጀት ጭምር ነው፡ የቤተ ክርስቲያናችንን መጠንከርና መስፋፋት የምንፈልገው። “ይህ፡ እንዴት ይኾናል?” የሚል ጥያቄ እንደሚኖር አይጠረጠርም፤ ለዚህ፡ መልሱ፡ አጭር ነው።

በመጀመሪያ፡ ሰው ራሱ፡ በተፈጥሮ ባሕርዩ ከሚደርስበት በላይ፡ በተለይ፡ በዛሬው ዘመን፡ ራሱ፡ ከራሱ ጋር የሚዋጋበት፡ የጦርነት መስክ ኾኗል። ይኸ የመሸበር፥ ይኸ የመታወክ፥ ይኸ የመጨነቅ ውጊያ፡ እንደምን ሊወገድለት ይቻላል? ይህን ለማስወገድ የሚችልበት፡ ሌላ እውቀት፥ ሌላ ጥበብ፥ ሌላ ሀብትና ሌላ ኃይል፡ ከቶ የለውም፤ እውቀቱና ጥበቡ፥ ሀብቱና ኃይሉ፡ አንድ ሃይማኖቱ ነው፤ እርሱም፡ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ይህን እውቀትና ጥበብ፥ ይህን ሀብትና ኃይል ለማግኘት የሚችለው ደግሞ፡ ከቤተ ክርስቲያኑ ብቻ ነው። አዎን! ያ ሰው፡ በሰውነቱ፥ በመንፈሱ ውስጥ ያለውን መሸበር፥ ያለውን መታወክና ያለውን መጨነቅ አስወግዶ፡ ጸጥታን፥ ሰላምንና ዕረፍትን የሚያገኘው፡ እውነተኛ ክርስቲያን፥ መልካም ምእመንና ታማኝ አገልጋይ ሲኾን ብቻ ነው።

ሰው፡ በዚህ ዓለም ያለው፡ የአጭር ዘመን ዕድሜው፡ ከአርባ፥ ቢበዛ፡ ከስድሳና ከሰባ፥ እጅግ ቢበዛ፡ ከሰማንያ ዓመታት አያልፍም፤ በዚህ በተወሰነች ዕድሜ፡ ፍጹም ሰላምንና ደስታን ካላገኘ፡ መፈጠሩና መኖሩ፡ ከቶ ለምን ይረባዋል? ለምን ይጠቅመዋል? እንግዴህ፡ ስለዚህ ነው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በተቻለ መጠን፡ በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ዘመን፥ ይህም፡ የተወሰነ፡ አጭርም ቢኾን፥ በዚያው ዕድሜው፡ ፍጹም ሰላምን፥ ጸጥታንና ደስታን፥ ዕረፍትንም ለማግኘት እንዲችል ነው፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ትጠንክር፥ ትስፋፋ የምንለው።

ዳግመኛም፡ ሰው፡ ብቻውን ሊኖር አይችልም፤ ብቻውንም እንዲኖር አልተፈጠረም፤ ኑሮውም፡ እንደአውሬ እንዲኾን አልተፈቀደም። በቤተሰብ፥ በጕርብትናና፥ በመንደር፥ ከፍም ሲል፡ በአገር ደረጃ እየተወሰነና እየተባበረ ይኖራል፤ በዚህ ዓይነት ማኅበራዊ ሥርዓት መኖር ግዴታው ነው።

ነገር ግን፡ ሰው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ እንደግል ሰውነቱ ኹሉ፡ ማኅበራዊ ኑሮውም እንዲሁ፡ ሁከት፥ ጭንቀት፥ ፀብና ክርክር የሌለበት፡ የፍቅር፥ የሰላምና የጸጥታ ሊኾን የሚችለው፡ ስለፍቅር የምታስተምር፥ ሰው ኹሉ፡ የተፈጥሮ ወገኑን፡ እንደራሱ እንዲወድ የምታስችል፡ “ሃይማኖት” የተባለችውን ፍቱን መድኃኒትና ኃይል፡ መሣሪያ አድርጎ የያዘ እንደኾነ ብቻ ነው።

ስለዚህ ነው፡ ማኅበራዊ ኑሮአችን፡ ሰላማዊ፥ የፍቅርና የጸጥታ እንዲኾን ለማስቻል፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ትጠንክር፥ ትስፋፋ የምንለው።

"ቤተ ክርስቲያን"፡ የካህናትና የምእመናን ጉባኤ ማለት መኾኑን፡ ራሱ፡ ስሙ ያመለክታል። እንዲህ ከኾነ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ልትጠነክር፥ ልትስፋፋ የምትችለው እንዴት ነው? ምን ብናደርግ ነው? ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ ኾኖ፡ ይህ፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ ተሰጥቷል።

አንድ ቤት፡ ዕድሜና ጽናት ሊኖረው የሚችለው፡ መሠረትና ግድግዳ እንደኾነው፡ እንደድንጋዩና እንደጡቡ፥ ወይም፡ እንደእንጨቱ ዓይነትና ጥራት እንደመኾኑ መጠን፡ ቤተ ክርስቲያናችንም፡ ልትጠነክርና ልትስፋፋ የምትችለው፡ ግድግዳ ኾነው ያቆሟት ካህናትና ምእመናን፡ በክህነታቸውና በምእመንነታቸው፡ እውነተኞችና ታማኞች ኾነው ሲገኙ ብቻ ነው።

ስለዚህ፡ እኛም፡ እያንዳንዳችን፡ በየግላችን፥ በኅብረተሰባችንና በአገራችን፡ የፍቅር፥ የሰላምና የደስታ ኑሮን ለመኖር የምንችለው፡ በወጣው የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ መሠረት፡ ቤተ ክርስቲያናችን የምትጠነክርበትንና የምትስፋፋበትን ተግባር የፈጸምን እንደኾነ ብቻ ነው።

የቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን፥ እኛም፡ ዛሬ፡ በግልም፥ በማኅበርም፡ በሰላም፥ በጸጥታና በነጻነት ለመኖር የቻልነው፡ ለምን እንደኾነ፡ መዘንጋት የለብንም፤ አዎን! በዚች ሃይማኖታችን ነው። እንዲህ፡ በሃይማኖታችን ኃይል ለመኖር እንደቻልን ኹሉ፡ ወደፊትም፡ በየግላችንም ኾነ፡ በማኅበራዊ ኑሮአችን፥ ለአገራችንም፡ ዋስትና ያለውን ሕይወት ለማስገኘት የምንችለው፡ በዚሁ የሃይማኖታችን ባለአደራ በኾነችው፡ በቤተ ክርስቲያናችን ኃይል መኾኑን እንዳንረሳው ያስፈልጋል። ለዚህ ነው፡ ቤተ ክርስቲያናችን ትስፋፋ፥ ትጠንክር የምንለው።

ይህ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ፡ ሲያያዝ የመጣውን፡ ሥርዓትና ባህል በመከተል፡ ዛሬ ላለችውና ወደፊትም ለምትቀጥለው ቤተ ክርስቲያን፡ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ መኾኑ ታውቆና ተረጋግጦ የወጣ መኾኑን፡ ካህናትም፥ ምእመናንም፡ ሊረዱት ይገባል። "ቤተ ክርስቲያን" ማለት፡ ሕንፃው፥ ግንቡ ሳይኾን፡ የካህናቱና የምእመናኑ አንድነት፥ ማኅበራቸው መኾኑ፡ ከላይ ተገልጿል። እንግዴህ፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን ደንብ፡ በሥራ ላይ ውሎ፡ ውጤት እንዲሰጥ ቢደረግ፡ ተጠቃሚው ማነው? ካህናቱና ምእመናኑ ናቸው።

ካህናቱ፡ ችሎታቸው፡ ይሻሻላል፤ አገልግሎታቸው፡ ይታወቃል፤ አስተዳደራቸው፡ ይቃናል፤ መብታቸው፡ ይጠበቃል፤ ለየራሳቸውና ለየቤተሰባቸው ትዳር የሚያስፈልጋቸው መተዳደሪያ፡ በሚበቃ ይወሰናል፤ የቆየ ክብራቸው ይታደሳል፤ ከምእመናን ጋር ያላቸው ግንኙነት፡ ጤናማ ኾኖ ይጠናከራል።

በዚህ መልክ፡ በደንቡ ውስጥ ተዘርዝሮ እንደተመለከተው፡ እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ የነበረውና ወደፊት ሊኖረው የሚችለው የገቢ ምንጭ፡ በሚገባ የተጠበቀ እንደኾነ፡ ይህ፡ የተሰበሰበውና የተጠበቀው ገንዘብ፡ በቅድሚያ፡ የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ዓላማዎች የኾኑትን፡ መንፈሳዊ አገልግሎትን፥ ትምህርትንና ስብከትን፥ ሌሎችንም፡ የበጎ ሥራና የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎቶችን፡ ለሕዝብ በመስጠት ላይ ለሚገኙት ካህናት፡ ከአገልግሎታቸው ጋር የሚመጣጠን የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው ስለሚደረግ፡ ደንቡ፡ በሥራ ላይ እንዲውል፡ ካህናትም፥ ምእመናንም፡ በኅብረት ሊያስቡበትና ሊጥሩበት የሚገባ ነው።

ምእመናኑም፡ በግልም፡ ኾነ በኅብረት፡ በካህናቱ አማካይነት፡ ከቤተ ክርስቲያን የሚጠብቁትና የሚፈልጉት አገልግሎት ኹሉ፡ የተሟላ ይኾናል፤ የየግላቸው፥ የቤተሰባቸውና የማኅበራዊ ኑሮአቸው፡ የሰላምና የጸጥታ፥ የደስታም ይኾንላቸዋል፤ አንድነታቸው ይጠነክራል፤ በደንቡ ውስጥ እንደተመለከተው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ በሥርዓት ተመዝግቦ ለታወቀ ምእመን፡ ማናቸውም ዓይነት አስፈላጊና መደበኛ የኾነው መንፈሳዊ አገልግሎት፡ ቅድሚያ ተሰጥቶት፡ ያለዋጋ፡ በነጻ ይፈጸምለታል።

ለእርሱም ኾነ፡ በእርሱ ኃላፊነት ሥር ለሚገኙት ቤተሰቦቹ፡ ከልደተ ሥጋ ጀምሮ፡ እስከሞተ ሥጋ ድረስ ያለው፡ የዚህ ዓለም ሕይወት፡ የተሟላና የተደላደለ እንዲኾንለት፡ በጸሎትና በመንፈሳዊው አገልግሎት ብቻ ሳይኾን፡ በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ ተገቢው፡ ሥጋዊ ፍላጎቱ፡ ተሟልቶ እንዲቀርብለት በማድረግ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ የኃላፊነት ድርሻዋን ታበረክትለታለች። በዚህ ዓለም ኾነ፡ በሚመጣው ዓለም፡ የዘለዓለም ሕይወትንና ዕረፍትን የሚያገኝ መኾኑን እያረጋገጠችለት፡ ለሥጋዊው ህልውናው፡ አስተማማኝ መጠጊያና ማረፊያ ትኾነዋለች።

ስለዚህ ነው፡ ካህናትም፥ ምእመናንም፡ ቤተ ክርስቲያን፡ የራሳቸው፥ በራሳቸውና ለራሳቸው መኾኗን አውቀው፡ በዚህ የሰበካ አስተዳደር ደንብ መሠረት፡ እንዲሠራበት ሊያደርጉ ይገባል የሚባለው።

## የቤተ ክህነት፡ ጠቅላላ የአስተዳደር አቋም።

በኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት መሠረት፡ ቤተ ክህነት፡ ከጥንት ሲያያዝ የመጣው አስተዳደርዋ፡ ከአጼው የበላይ ጠባቂነት ጀምሮ፡ እስከእጨጌው መሪነትና እስከቤተ ምልክናው ባለሥልጣኖች የድጋፍ ተባባሪነት ድረስ፡ ካህናቱ፡ ከውስጥ፥ ምእመናኑ፡ ከውጭ፡ የሚያስፈልጋትን አገልግሎት ኾነ፡ ሀብት በመስጠት፡ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀዋት ኖረዋል።

የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ፡ በይበልጥ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ እንደመኾኑ፡ የቤተ ክህነት ጠቅላላ የሥራ አቋምና አመራር ተጠብቆ፡ በትክክልና በሥርዓት እንዲካኼድ የሚያደርግ፡ "የቤተ ክህነት ጉባኤ" ተብሎ የሚጠራ አንድ አካል አለ። ይህ አካል፡ እንዳስፈላጊነቱ፡ በየጊዜያቱ የሚሰበሰቡ፡ ኹለት ቅርንጫፎች አሉት፤ አንደኛው፡ ሊቃነ ካህናቱ (Papasat) አባሎች የኾኑበት "ሃይማኖታዊ ሕዋስ" (Synod) የሚባለው ሲኾን፥ ኹለተኛው ደግሞ፡ በእጨጌው አቅራቢነት፡ በአጼው የሚሾሙ፡ ከቤተ ክህነቱ፥ ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው የተውጣጡ፡ ቁጥራቸው የተወሰነ ካህናትና ምእመናን፡ በአባልነት የሚገኙበት፡ "ምግባራዊ ሕዋስ" የሚባለው ነው።

የቤተ ክህነቱ ጉባኤ፡ በእጨጌው ሊቀ መንበርነት፡ በዓመት፡ ቢያንስ፡ ኹለት ጊዜያት፡ በመደበኛነት እየተሰበሰበ፥ እንደሥርዓተ መንግሥቱም፡ በየጊዜው በወጡ ሕጎች መሠረት፡ ሃይማኖትንና ምግባርን፥ ሥርዓትንና ፍትሕን፥ ትምህርትንና አገልግሎትን በሚመለከቱ አርእስተ ነገሮችና ጉዳዮች ላይ፡ እየመከረና እየወሰነ፡ የውስጥ መመሪያዎችን፥ ደንቦችንና ሥርዓቶችን እያወጣ ይሠራል። ይህም፡ የነበረውን ብሔራዊ ሕግ ተከትሎ፡ በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. በቍጥር ፴፰ እና በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በቍጥር ፹፫፡ በነጋሪት ጦማረ ሕዝብ (Gazetta) የወጣው የትእዛዝ አዋጅ፡ ስለጠቅላላዋ ቤተ ክህነት፡ የአስተዳደር አመራርና የሀብት አጠባበቅ፡ ሙሉ የባለአደራነትና የኃላፊነት ሥልጣንን፡ ለዚሁ ጉባኤ የሰጠ በመኾኑ ነው።

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ ጥንታዊዉን የሥራ አመራርና የአስተዳደር ሥርዓት፡ በበለጠ ለማሻሻልና ለማቀላጠፍ ይረዳል ተብሎ የወጣው ሰብአዊ ሕገ መንግሥት፡ ይህንኑ፡ የባለአደራነትና የኃላፊነት ሥልጣን፡ እንደሚከተለው፡ በማረጋገጥ ይገልጠዋል፡-

ይኸውም፡

፩ኛ፡ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ፩፻፳፮ እና ፩፻፳፯ ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡

ሀ/ የኢትዮጵያ መንግሥት መሠረታዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመኾኗ፡ በመንግሥቱ የተደገፈች መኾኗን፥

ለ/ ድርጅቷና አስተዳደርዋ፡ በሕግ የሚመራ፥ በገዳማዊነት ኑሮና በመንፈሳዊ አስተዳደር፡ ካልኾነ በቀር፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር ደንቦች ለማወጅ፡ ርእሰ ብሔር የኾነው አጼ፡ ሥልጣን ያለው መኾኑን ነው፡፡

፪ኛ፡ ሕገ መንግሥቱን መሠረት አድርጎ በወጣው፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ፡ ስለመንግሥቱ የአስተዳደር ክፍሎችና ስለቤተ ክርስቲያን በተጻፉት አንቀጾች፡ ቍጥር ፫፻፺፰፥ ፫፻፺፱ እና ፬፻፥

ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በሕግ በኩል፡ እንደአንድ ሰው የምትቈጠርና እንዲህ በመኾኗ፡ በመሥሪያ ቤቶቿ አማካይነት፡ በአስተዳደር ሕጎች የተፈቀዱትን መብቶች ኹሉ፡ ልታገኝና ልትሠራባቸው የምትትችል መኾኗ፥

ለ/ እንዲሁም፡ የቤተ ክርስቲያን ክፍል የኾኑ፡ የሀገረ ስብከት፥ አድባራትና ገዳማት፡ በሕግ በኩል፡ ግዴታ ያለባቸውና መብት ያላቸው መኾናቸው ተመልክቷል፡፡

፫ኛ፡ አጼው፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስፈልገውን፡ የአስተዳደር ደንቦች ለማወጅ፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፩፻፳፮ እንደተመለከተው፡ ባለው ሥልጣን መሠረት፡ በ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. በነጋሪት ጦማር ታትሞ ከወጣው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ ጋር፡ በቅርቡ፡ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ አስተዳደር፡ በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. በነጋሪት ጦማር ታትሞ የወጣ፡ ቁጥር ፵፰ የትእዛዝ አዋጅንና ይህንኑም በማሻሻል፡ በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. በነጋሪት ጦማር ታትሞ የወጣ፡ ቁጥር ፹፫ ማሻሻያ ትእዛዝን፡ በይፋ ሰጥቷል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መምሪያና ማሻሻያ እንዲኾን፡ ይህ የትእዛዝ አዋጅ፡ በአጼው፡ የተሰጠበት ምክንያት፡ በአዋጁ መቅድም ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ እርሱም፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፡
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡
ሥዩመ እግዚአብሔር፡ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፡፡

አዲሱን የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈሳዊ ፍላጎት ለማርካት፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት እያደገ መኼዱን በመመልከት እና በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችንና እንዲሁም፡ ስለቤተ ክርስቲያን ንብረት አጠባበቅ፡ በፍትሓ ብሔር ሕግ በተወሰነው መሠረት፡ ቤተ ክርስቲያኗ፡ አማንያንን፡ በሚገባ ለማገልገል እንድትችል፡ ተጨማሪ ሥልጣን እንዲኖራት ማድረግ፡ አስፈላጊነቱን በመረዳት፡ በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን፡ አንቀጽ ፩፻፳፮ እና በፍትሓ ብሔር ሕግ፡ አንቀጽ ፫፻፺፰ እና ፬፻ መሠረት፡ ቀጥሎ ያለውን አዘናል፤" ይላል፡፡

በእነዚህ የትእዛዝ አዋጆች ውስጥ፡ የቤተ ክህነት ጉባኤ፡-

ሀ/ ቤተ ክርስቲያን፡ የምእመናኗን ፍላጎት ለማሟላት፡ በምትችልበት አኳኋን፡ ሥጋዊ አስተዳደርዋን ለመምራት፥ ለመጠበቅና ለማሻሻልም፡ አስፈላጊና ጠቃሚ ኾኖ የተገኘውን ተግባር ለመፈጸም፥ በተለይም፡ ከዚህ በላይ፡ በጠቅላላ መልክ፡ በተጠቀሰው ብቻ ሳይወሰን፡ የቤተ ክርስቲያን ባለአደራ ኾኖ፡ የሀብትና የንብረት አስተዳደሩንም ሥራ ለማከናወን፥ እንዲሁም፡ በዚሁ ትእዛዝ፡ በዝርዝር በተመለከተው፥ ወይም፡ በሕግ በተፈቀደለት ሌላ ሥልጣን መሠረት፡ ሥራውን በሚያካኼድበት ጊዜ፡ አስፈላጊውን፥ ወይም፡ ግዴታው ኾኖ ያገኘውን፡ ማናቸውንም፡ ሕጋዊ አድራጎት ለመፈጸም፡ ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ሲኾን፥

ለ/ በሕግ በተወሰነው መሠረት፡ ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ስለአፈጻጸሙም፡ በቤተ ክህነቱ፡ ነጋሪት ጦማር፡ ደንብ ለማውጣት የሚችል መኾኑ ተመልክቷል፡፡ ከጥንት ሲያያዝ በመጣውም ኾነ፡ በተለይ፡ በዘመናዊው የአስተዳደር አመራር፡ ያለው፡ የሥልጣንና የሥራ መደብ፡ በሦስት ተከፍሎ፡ የተደላደለ ሲኾን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም አቋም፥ አስተዳደርና የሥራ አመራር፡ ይህንኑ የተከተለ ነው፡፡ ይህም፡

፩. በእጨጌው ሊቀ መንበርነት፡ በቀኖናዎችና መንፈሳውያን በኾኑ፥ እንዲሁም፡ በአስተዳደርና በሥራ ጉዳዮች ላይ እየመከረ፡ ውሳኔ የሚሰጥና ደንቦችን የሚያወጣ፡ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለሥልጣን አካል የኾነውን፡ የቤተ ክህነት ጉባኤን፥

፪. በዚሁ፡ በቤተ ክህነቱ ጉባኤ የወጡትን ደንቦች፥ የተሰጡትን ውሳኔዎችና ትእዛዞችም፡ በሥራ ላይ ዐውሎ የሚፈጽመውን፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የሚመራውን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትን፥

፫. በሃይማኖታዊውና በአስተዳደር ረገድ፡ አከራካሪ ኾነው የተገኙ ጉዳዮችን፡ በጻኝነት መልክ እየመረመረ፡ ብይንና ፍርድ የሚሰጥ፡ ፍትሕ መንፈሳዊን አካትቶ የያዘ ነው፡፡

በዚህ ጠቅላላ መልክ የተገለጸው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ሥራ፡ አመራሩና አፈጻጸሙ ቀና ይኾን ዘንድ፡ በሚከተለው ኹኔታ፡ በተዋረድ ተከፋፍሎ ይካኼዳል፡- የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ መላውን፡ የቤተ ክርስቲያንን፡ የአስተዳደርና የሥራ አመራር፡ ኀላፊነትና ተግባር፡ አጠቃልሎ የያዘ ሲኾን፡ እያንዳንዳቸው፡ በአንዳንድ ብፁዓን ሊቃነ ካህናት የበላይነት የሚመሩና በአንዳንድ ዋና ሥራ አስኪያጆች የሚተዳደሩ፡ የሀገረ ስብከት መሥሪያ ቤቶች፡ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ተቋቁመው ይገኛሉ፡፡ እነዚህም፡ ከአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ጋር፡ ቁጥራቸው፡ አሥራ አምስት መኾኑ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት፡ በአውራጃዎች፥ እያንዳንዱም አውራጃ፡ በሰበካዎች ተከፋፍሎ፡ አስተዳደሩና ሥራው፡ ኀላፊነት ባላቸው ተጧሚዎችና ሠራተኞች ይካኼዳል፡፡ ከእነዚህ፡ ጋር፡ የአንድነት ገዳማት፥ እንዲሁም፡ ከኢትዮጵያ ውጪ፡ በኢየሩሳሌም፥ በዌስት ኢንዲስ፥ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ፥ በዓለም ልዩ ልዩ አህጉርም ተመሥርተው የሚካኼዱት ገዳማትና የሰበካ አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ፡ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላላ አቋም፥ አስተዳደርና የሥራ አመራር፡ ይህን፡ ከዚህ በላይ፡ በአጭር የተወሰነውን መግለጫ ከሰጠን፡ የቤተ ክርስቲያን፡ ብቸኛው መሠረታዊ መነሻ ስለኾነው፡ የሰበካ ጉባኤ አቋቋም፥ ዓላማና ተግባር የሚከተለው ዝርዝር መግለጫ ቀርቧል፡፡

# የቤተ ክርስቲያን ሰበካ አስተዳደር፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው፡ "ቃለ አዋዲ" በተባለው፡ የቤተ ክህነት የደንብ ጦማረ ሕዝብ ላይ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ በወጣው ደንብ መሠረት፡ በሕግ ተቋቁሟል፡፡

"ቃለ አዋዲ" የተባለው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት የደንብ ጦማረ ሕዝብ የተቋቋመው፡ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፡ በቁጥር ፺፫/፲፱፻፷፮ ዓ. ም. በመንግሥቱ ነጋሪት ጦማረ ሕዝብ፡ ታትሞ በወጣው ማሻሻያ ትእዛዝ ሲኾን፡ የቤተ ክህነት ጉባኤ፡ በዚሁ፡ የደንብ ጦማረ ሕዝብ አማካይነት የሚያወጣቸው ደንቦችና ውሳኔዎች፡ ሕጋዊነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ በዚህ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፡ እነዚህን ደንቦችና ውሳኔዎች፡ በይፋ ለመግለጽና በሕግ ለማስታወቅ፡ በጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ ተጠባባቂነት፡ ይህን የደንብ ጦማረ ሕዝብ፡ እየተቀጣጠረ፡ በየጊዜያቱ ያወጣል፡፡

የቤተ ክህነቱ ሕጋዊ የደንብ ጦማረ ሕዝብ በኾነው፡ በዚሁ "ቃለ አዋዲ"፡ በ፩ኛው ዓመት፥ ቁጥር ፩ ታትሞ የወጣው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ደንብ፡ እያንዳንዱን ካህንና ምእመን፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር፥ ሀብትና ሥራ አመራር፡ ቀጥተኛና ግልጽ በኾነ መልክ፡ የሥልጣንና የኃላፊነት ተካፋይነት እንዲኖረው የሚያደርጉ፡ የመብትና የግዴታ አንቀጾች ስላሉበት፡ እነዚህን አንቀጾች፡ እያንዳንዱ ካህንና ምእመን፡ ደህና አድርጎ እንዲያውቅ ማድረግ፡ አስፈላጊ ስለኾነ፡ ስለእያንዳንዱ አንቀጽ፡ እንደሚከተለው ዝርዝር ማብራሪያን እንሰጣለን፡፡

## የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ደንብ አንቀጾች
## ማብራሪያ፡፡

<u>ስለ፩ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ይህን የሰበካ አስተዳደር ደንብ ለመስጠት፡ በሕግ ሥልጣን ያለው፡ የቤተ ክህነት ጉባኤ መኾኑን፥ ይህም የቤተ ክህነት ጉባኤ፡ ይኸን ሥልጣን ያገኘው፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በነጋሪት ጦማረ ሕዝብ፡ ቁጥር ፵፫/፲፱፻፶፱ ዓ. ም. እና ቁጥር ፹፫/፲፱፻፷፮ ዓ. ም. በወጣው ማሻሻያ ትእዛዝ መኾኑን ያመለክታል፡፡

በእነዚህ፡ በትእዛዙና በማሻሻያው ትእዛዝ የተጠቀሱት ሥልጣናት ሲነበቡ፡-

ሀ/ የቤተ ክህነት ጉባኤ፡ ስለጠቅላላው የቤተ ክርስቲያኗ ሥጋዊ አስተዳደርና ስለጉባኤው ሥራ አፈጻጸም፡ አስፈላጊና ተገቢ መስለው የታዩትን ሥርዓቶችና ደንቦች፡ ሊያወጣ ይችላል፤

ለ/ እጨጌው፡ በቤተ ክህነቱ ጉባኤ አሳሳቢነት፡ በዚህ ትእዛዝ የተመለከተውን ለማስፈጸም፡ በቤተ ክህነት ጦማረ ሕዝብ፡ ደንብ ለማውጣት ይችላል፤" ይላል፡፡

<u>ስለ፪ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ደንቡ፡ በተለይ የሚጠራበትንና የሚጠቀስበትን ስም የሚገልጽ ነው፡፡

ስለ፫ኛው አንቀጽ፡-

ይህ አንቀጽ፡ "የሰበካ ጉባኤ"፡ ምን ማለት እንደኾነ፡ ባጭር ይተረጉማል፤ የትርጓሜው አንቀጽ በዝርዝር ሲተነተን፡-

ሀ/ "ሰበካ" የሚባለው፡ በአንድ ገዳም÷ ደብር፡ ወይም፡ ገጠር በኾነ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኝ መንፈሳዊ ክልል ነው።

ለዚያ ክልል የተመደበው ካህን፡ ያለበት ኃላፊነት፡ እስከምን ድረስ እንደኾነ÷ አገልግሎት የሚሰጠውስ ለማን እንደኾነ፡ ማወቅ ይኖርበታል። ካህኑ፡ መንፈሳዊ እረኛ÷ መንፈሳዊ ሓኪምና መንፈሳዊ አገልጋይ ስለኾነ፡ በዚህ ኃላፊነቱ የሚጠብቃቸው መንጎች÷ የሚፈውሳቸው ሕሙማንና የሚያገለግላቸው ምእመናን፡ የት እንደሚገኙ÷ እነማን እንደኾኑ፡ አንድ በአንድ፡ ስማቸውን (የክርስትናውን) ጭምር ለይቶ ማወቅ ግዴታው ነው።

በዚያ ክልል የሚኖረው ምእመንም፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚያገኝባት÷ የሚገለገልባትና የሚያገለግላት÷ ከነፍስና ከሥጋ ድካም የሚያርፍባት፡ የዘለዓለም ቤቱ፡ የትኛዋ እንደኾነች፡ ማወቅ ይኖርበታል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"የበጎች እረኛ እኔ ነኝ! መንጎቼን አውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ ድምፄን ሰምተው ይከተሉኛል፤"** ብሎ እንደተናገረው፡ የጌታ መልእክተኛና ተጠሪ የኾነው ሓዋርያው ካህን፡ እንደቸር እረኛ÷ መንጎቹም ምእመናን፡ የካህናቸውን ድምፅ ለይተው የሚያውቁና የሚከተሉት መኾን ይገባቸዋል። (ዮሐ. ፲÷ ፩-፲፮።)

ይህን ለማድረግና ስለሰበካ ጉባኤ አስተዳደር፡ በወጣው ደንብ መሠረት ለመሥራት፡ በቅድሚያ፡ የእያንዳንዱ ሰበካ ክልልና ወሰን፡ በግልጽ ተለይቶ ሊታወቅና ሊረጋገጥ ያስፈልጋል። የዚህ የሰበካ ክልልና ወሰን፡ በትክክል ተለይቶ እንዲታወቅና እንዲረጋገጥ የማድረጉ ተግባር፡ ከማናቸውም ሥራ ይልቅ፡ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ፡ ዋና ጉዳይ ነው።

ይኹን እንጂ፡ የሰበካዎች ክልል፡ ለኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ እንግዳ ነገር ኾኖ፡ እንደአዲስ የሚቋቋም አይደለም፤ ቤተ ክርስቲያን በተተከለበት ሥፍራ ኹሉ ያለ ነው። አኹን የሚያስፈልገው፡ በከተማም ቢኾን÷ በገጠርም ቢኾን፡ ያለውንና የነበረውን የሰበካ ክልል፡ እንዲጸና ማድረግ ነው። ምናልባት፡ በዚህ ረገድ፡ አስቸጋሪ ኹኔታ ቢያጋጥም፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ ጉዳዩን፡ ለክፍሉ አውራጃ ቤተ ክህነት አቅርቦ ማስወሰንና ማስፈጸም ይችላል።

ለ/ "የሰበካ ጉባኤ" የሚባለው፡ ከላይ በሀ/ ተራ ፊደል እንደተገለጸው፡ ወሰኑ ተከልሎ በታወቀ አጥቢያ ውስጥ የሚኖሩ÷ ዕድሜያቸው፡ ከሃያ አንድ ዓመታት በላይ ኾኖ፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተመዝግበው፡ የመምረጥና የመመረጥ መብት የተሰጣቸው ካህናት÷ የታወቁ ወንዶችና ሴቶች ምእመናንም የሚገኙበት ማኅበር ነው። ስለዚህ፡ "የሰበካ ጉባኤ" ሲባል፡ በሰበካው ውስጥ የሚኖሩትን፡ መላውን ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ያጠቃለለው ማኅበር ማለት ነው።

ስለ፬ኛው አንቀጽ፡-

ይህ አንቀጽ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ የአስተዳደር፡ በሕግ፡ ራሱን ችሎ የተቋቋመ መኾኑን የሚያረጋግጥ ነው። ማናቸውም መሥሪያ ቤት÷ ድርጅት÷ ወይም፡ ማኅበር፡ በሕግ የታወቀ ኾኖ፡ በተቋቋመበት ዓላማ፡ መሥራት የሚችለው፡ አስቀድሞ፡ በሕግ፡ የሰውነት መብት የተሰጠው ሲኾን ነው።

በዚህ መሠረት፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክፍል የኾኑ አድባራትና ገዳማት፡ በሕግ በኩል፡ ግዴታ ያለባቸውና መብት ያላቸው መኾናቸው፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ የተረጋገጠ ሲኾን፡ ለቤተ ክህነት በተሰጣት ሥልጣን መሠረት፡ እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ ራሱን የቻለ ድርጅት ኾኖ ለመሥራት የሚችልበት፡ የአስተዳደር ደንብ የተሰጠው መኾኑን፡ ይህ አንቀጽ ይገልጻል፡፡

እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ በዚህ ዓይነት፡ በሕግ፡ ራሱን የቻለ፡ አቋምነት የተሰጠው ኾኖ ይቋቋም እንጂ፡ በሕጎችና በአስተዳደሩ ደንብ ውስጥ በተመለከተው መሠረት፡ እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ ባለበት የሀገረ ስብከት አስተዳደር የበላይ መሪነትና ተቆጣጣሪነት ሥር የሚገኝና በደንቡ ውስጥ ለተመለከተው አሠራር፡ የሚፈለግበትን ግዴታዎች፡ መፈጸም የሚኖርበት መኾኑ መታወቅ አለበት፡፡

እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ ለመጻጻፍና ለሌላውም ተግባሩ፡ ለየራሱ መታወቂያ የሚኾነው፡ የተለየ አርእስትና ማኅተም እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ ይህም አርእስትና ማኅተም፡ እንደሚከተለው ይኾናል፡-

"በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የ...(የጠቅላይ ግዛቱ ስም ይጻፋል)...ሀገረ ስብከት÷ የ...(የከተማው÷ ወይም፡ የገጠሩ ስም ይጻፋል)÷ የ...(የቤተ መቅደሱ ልዩ ስም ይጻፋል) ሰበካ" ተብሎ ይጻፋል፡፡

ለምሳሌ፡- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን÷
የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት÷
የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ሰበካ፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን÷
የኤርትራ ሀገረ ስብከት÷
የአሥመራ ደብረ ጽዮን ማርያም ሰበካ፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን÷
የሓረርጌ ሀገረ ስብከት÷
የሓረር ጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ሰበካ፡፡

እንደማለት ነው፡፡

## ስለ፫ኛው አንቀጽ፡-

ይህ አንቀጽ፡ የሰበካው ጉባኤ የተቋቋመበትን ዓላማ እንደሚተለው ይዘረዝራል፡-

ንዑስ አንቀጽ ፩፡ በካህናት በኩል፡ ለምእመናን የሚደረገው መንፈሳዊ አገልግሎት ተስፋፍቶ፡ ለኹሉም እንዲዳረስ የሚያመለክት ነው፡፡ እዚህ ላይ፡ "መንፈሳዊ አገልግሎት"፡ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፡ እነማን እንደኾኑ፡ መዘርዘር ያስፈልጋል፤ እነዚህም፡ ምሥጢረ ጥምቀት÷ ምሥጢረ ሜሮን÷ ምሥጢረ ቊርባን÷ምሥጢረ ክህነት÷ ምሥጢረ ንስሓ÷ ምሥጢረ ተክሊልና ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው፡፡

እነዚህን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም÷ እንዲሁም፡ በሌሊት÷ በጠዋትና በማታ÷ በማናቸውም ጊዜ የሚካኼዱ የሰዓታት÷ የማኅሌትና የቅዳሴ÷ ሌሎችም፡ ጸሎተ ፍትሐትን የመሰሉ፡ ብዙ የጸሎት ሥርዓቶች አሉ፡፡

እነዚህ ኹሉ፡ በምእመናኑ ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ባለው፡ በሚመችና በሚስማማ ኹኔታ፡ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንደሚፈቅደው፡ መፈጸም አለባቸው፡፡

ይህን በመሰለው መልክ፡ ከላይ የተጠቀሱትን መንፈሳውያን አገልግሎቶች፡ ለምእመናኑ የሚያበረክቱት፡ ካህናቱ ሲኾኑ፥ እኒሁ ካህናት ደግሞ፡ እነዚህን መንፈሳውያን አገልግሎቶች፡ ለምእመናኑ ለማበርከት፡ ንቃትና ትጋት፥ ችሎታና ብቃት ያላቸው እንዲኾኑ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በላይ ስለተዘረዘሩት፡ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራትና ሥርዓታት፥ ስለሌሎችም የጸሎት ሥርዓቶች፥ እንዲሁም፡ ስለካህናቱ ችሎታ መሟላትና ስለአገልግሎታቸው ጠቅላላ ኹኔታ፡ በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የመንፈሳዊው አገልግሎት መምሪያ፡ ተገቢውን እያጠና፡ በየጊዜው፡ አስፈላጊውን የውስጥ ደንብና መመሪያ ይሰጣል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፪፡ በሰበካው ክልል ውስጥ፡ የኢትዮጵያዊነትና ዘመናዊው ትምህርት ጭምር የሚሰጥበት፡ አንድ፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡ የሙያ ማሠልጠኛ ዘርፍ ያለው ኾኖ እንዲቋቋም ያስፈልጋል፤ የተቋቋመም ካለ፡ በዚህ መልክ መደርጀት ይኖርበታል፡፡

ይኸው ትምህርት ቤት፡ የሕፃናት ማሳደጊያና ማስተማርያ፥ እንዲሁም፡ ከ፩ኛ እስከ፬ኛ፥ ወይም፡ እስከ፮ኛ እና እስከ፰ኛ ክፍል ድረስ ያለው ኾኖ፡ ከአንደኛ ደረጃ ማዕርግ የሚደርስና ለምእመናኑ በማይከብድ መጠን የሚከፈልበት፥ ዓቅም የሌላቸው ግን፡ ኹኔታቸው እየተጣራ፡ በነጻ የሚማሩበት ሊኾን ይገባል፡፡ የትምህርት ቤቱ ክፍልና ደረጃ፡ ዓቅም በፈቀደ መጠን፡ እንዳስፈላጊነቱ እያደገ፡ እስከኹለተኛ ደረጃ ሊደርስ እንዲችል ማድረግ፡ አግባብ ይኾናል፡፡

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፥ ሥርዓተ ትምህርቱ፥ የማስተማሪያው መጻሕፍትና የመምህራኑ የሙያ ደረጃ፡ በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ እየተጠናና እየተዘጋጀ በሚወጣው፡ የውስጥ ደንብና መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፫፡ በየቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ፡ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት አለበት፤ በስብከተ ወንጌል አማካይነት፡ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት፡ ለሕፃናት፥ ለወጣቶችና ለታላላቆች፡ ለወንዶችም፥ ለሴቶችም፡ በየመልኩ እንዲሰጥ ያስፈልጋል፡፡

በሰበካው ክልል ውስጥ ባሉ፡ በልዩ ልዩ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመገኘት፡ ለሕፃናትና ለወጣቶች፡ ጧትና ማታ፡ በሰልፍ ላይ ሣሉ፡ ጸሎትና ስብከት በማድረግ፥ በእነዚህም ትምህርት ቤቶች፡ የወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ክበቦችን በማቋቋም፥ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደግሞ፡ የሰንበት ትምህርትንና የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበሮችን በመመሥረት፥ ታላላቆቹን ወንዶችና ሴቶችንም፡ በሰበካው ክልል ውስጥ በሚገኙ፡ ዕድሮች፥ የጽዋና የሰንበት ማኅበሮች አማካይነት በመቅረብ፥ እንዲሁም፡ በተለያዩ ስብሰባዎች፥ በይበልጥም፡ ሕዝቡ፡ በብዛት በሚወጣባቸው፡ በቀብርና በሠርግ ሥርዓቶች ላይ፡ ያለማቋረጥ ሳይለዩ በመገኘት፡ ከፍተኛ ውጤት ያለው ጠቃሚ ትምህርት መስጠት፥ የስብከተ ወንጌል መልእክትም ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

በሰበካው ክልል ውስጥ በሚገኙ የሕክምና ቤቶችና ወህኒ ቤቶች፥ የሕግ ዘበኛና ልዩ ልዩ የመከላከያ ኃይላት ሠፈሮች ውስጥ፡ ቋሚ መምህረ ንስሓ በሚኾኑ ቀሳውስት አማካይነት፡ ይህንኑ ተግባር ማካኼድና መፈጸም፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ግዴታ ነው፡፡

በሰበካው ክልል ውስጥ፡ ልዩ ልዩ ባዕድ ሃይማኖትን ለማስፋፋት የሚሞክሩ ተቃዋሚ ወገኖች ቢኖሩ፡ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ መከላከልና መንጎችን ከነጣቂ ተኩላ ለማዳን፡ የሚቻለውን ኹሉ ማድረግ አግባብ ይኾናል፡፡ ይህን የመሰለውን ግዳጅ ለመፈጸም የሚያስችል፥ ለስብሰባና ለስብከተ ወንጌል መስጫ የሚያገለግል፡ አንድ ራሱን የቻለና የተሟላ ድርጅት ያለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡

በዚህ አዳራሽ ውስጥ፡ የሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ፥ እንዲሁም፡ ሰበካውንና የሰበካውን ነዋሪዎች ስለሚመለከቱ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ፥ ማኅበራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ለሚጠሩ ስብሰባዎች ይደረጉበታል፡፡ ጠቃሚና ትምህርት ነክ የኾኑ ንግግሮች፥ ውይይቶች፥ ዐውደ ጥናቶች፥ ተውኔቶችና ትርኢቶች ይካኼዱበታል፡፡ ሌሎችም፡ ይህን የመሰሉ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ይሰጡበታል፡፡

ከላይ፡ በአጠቃላይ እንደተገለጸው፡ ስብከተ ወንጌልን የማስፋፋትንና ማስታወቂያን የማሠራጨትን ዓላማና ተግባር በሚመለከት፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የስብከተ ወንጌልና የማስታወቂያ መምሪያ፡ አስፈላጊ የኾኑትን የውስጥ ደንቦችንና መመሪያዎችን በመስጠት፡ የአገልግሎት ግዳጁን ይፈጽማል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፬፡ በሰበካው ክልል፡ የማኅበራዊ ኑሮና የምግባረ ሠናይ አገልግሎቶች፡ በተቻለና ዓቅም በሚፈቅደው መጠን፡ መልክ ባለው ኹኔታ ተደራጅተው መሰጠት አለባቸው፡፡

"ምግባረ ሠናይ" የሚባለው፡ በጎ አድራጎት፥ ወይም፡ መልካም ሥራ ማለት ሲኾን፡ ይህም፡ በሰበካው ክልል ውስጥ፡-

ሀ/ እናት አባት፥ ጠባቂ፥ ደጋፊ ለሌላቸውና የሙት ልጆች ለኾኑ ሕፃናት ማሳደጊያ ቤትን፥

ለ/ ሕሙማንን፥ ደግሞም፡ ጤንነታቸውና አካላቸው ለጎደለ፥ ምንም ረዳትና ደጋፊ ለሌላቸው ደካሞች፡ በኑሮና በሕክምና የሚረዱበት ድርጅትን፥

ሐ/ በዕድሜ መግፋት ምክንያት፡ ሠርተው ማደር ለማይችሉትና ጧሪ ቀባሪ ለሌላቸው አዛውንት፥ ለሽማግሌዎቹም፥ ለአሮጊቶቹም፡ የመኖርያ ሠፈርን በማቋቋም መርዳት ነው፡፡

እነዚህ፡ ከላይ የተዘረዘሩት ደካሞችና ችግረኞች ኹሉ፡ ሊረዷቸውና ሊደግፏቸው የሚችሉ፡ በትውልድ፥ ወይም፡ በሕግ፡ ዝምድና ያላቸው ወገኖች እንዳሉ፥ ከሌሉም፡ በሰበካው ክልል ውስጥ ኾነ ከዚያ ውጪ፡ ለእነዚሁ ደካሞችና ችግረኞች፡ አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ ለማበርከት፡ በጎው ፈቃድና የሀብት ዓቅሙ ያላቸው ግለሰቦች፥ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መኖራቸውን፡ በቅድሚያ በማጣራት፡ በዚህ ረገድ፡ የሚተባበሩ ከተገኙ፡ እነዚህኑ ወገኖች፡ በዚሁ የበጎ አድራጎቱ ተግባር፡ እንዲሳተፉ ማድረግ ይቻላል፡፡

መ/ ከእነዚህ በቀር፡ ሙሉ ጤንነትና አካል እያላቸው፥ በዕድሜም፡ የበቁ ኾነው፡ መሥራት እየቻሉ፡ ነገር ግን፡ በሥራ ፈትነትና በስንፍና፥ በልመናና በሌላ ክፉ ልማድ ተመርዘው፡ በጎጂ ተግባር ላይ የተሠማሩ ቢኖሩ፡ እነዚህ ግለሰቦች፡ በሰበካው ውስጥ በሚቋቋመው የማሠልጠኛና የሙያ ዘርፍ ውስጥ ገብተው እንዲመከሩና እንዲታረሙ፥ በነጻ እንዲማሩና እንዲሠለጥኑ ከተደረገ በኋላ፡ ዓቅማቸው በሚፈቅደው መጠን፡ በየሠለጠኑበት ሙያ ተመድበው የሚያገለግሉበት ሥራ ይሰጣቸዋል፡፡

ከእነዚሁ ግለሰቦች መካከል፡ ከላይ የተመለከተው ዕድል ቀርቦለት፡ ምናልባት፡ ይህንኑ ተቀብሎ ለመፈጸም፡ ፈቃደኛ የማይኾን ቢገኝ፡ ይኸው ሰው፡ ለኢትዮጵያዊው ማኅበራዊ ኑሮ፡ ጠንቅ መኾኑን፡ ራሱ፡ በራሱ ማስታወቁ ነውና፡ የሰበካው አስተዳደር፡ የዚህኑ ሰው ኹኔታ፡ ከነጉዳዩ፡ ለሚመለከተው፡ የመንግሥቱ የቤተ ምልክና መሥሪያ ቤት አስታውቆ ማስተላለፍ አለበት፡፡

ሠ/ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚታዩትን፥ የሚካኼዱትንና የሚገኙትን፡ "የሕፃናትንና የወጣቶችን፡ የወንዶቹንም፥ የሴቶቹንም፡ መልካም አስተዳደግና ጠባይ፥ በጠቅላላም፡ ከፈጣሪያችን፡ በቃል ኪዳን የተረከብነውን፡ ኢትዮጵያዊ ያኗኗር ባህላችንን የሚቃረኑና የሚያበላሹ ናቸው!" ተብለው የሚገመቱትን ኹኔታዎች፥ ድርጊቶችና ተቋሞች ኹሉ፡ በተቻለ መጠን እንዲስተካከሉ፥ እንዲጸዱና እንዲለወጡ ማድረግ፥ ይህ የማይቻል ከኾነ ግን፡ ተገቢውን ይፈጽም ዘንድ፡ ጉዳዩን፡ ለሚመለከተው፡ የመንግሥቱ የቤተ ምልክና መሥሪያ ቤት በማሳሰብ፡ ማስተላለፍ፡ የሰበካው አስተዳደር ኃላፊነት ይኾናል፡፡

በማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓታችን ላይ ከባድ ጠንቅን የሚያስከትለውን፡ ይህን ዓይነቱን ችግር ለማሻሻልና ለማስወገድ የሚቻለው፡ ለሕፃናቱና ለወጣቶቹ፥ እንዲሁም፡ ለትልልቆቹ ወንዶችና ሴቶች ሳይቀር፡ ለኹሉም፡ እንደየደረጃው፥ እንደየወገኑና እንደየፍላጎቱ፡ የሚገባውን፡ የጊዜ ማሳለፊያ፥ የዕረፍት ማድረጊያና የመዝናኛ ሥፍራዎችን አሟልቶ በማደራጀት ጭምር መኾኑን ተረድቶ፡ ይህንኑ ድርጅት ማዘጋጀት፡ የሰበካው አስተዳደር ፋንታ ይኾናል፡፡

እንግዲህ፡ እያንዳንዱ ሰበካ፡ በዚህ መልክ አጥብቆ ከሠራ፡ ይህ ሥራ፡ በብሔር ደረጃ ሲጠቃለል፡ በአገራችን፡ የለማኞችና የድሆች ቁጥር፡ በምን ያህል መጠን ሊቀንስ፥ የችግረኞችና የደካሞች ሸክምም ሊቃለል፥ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆችም ኃይል ሊዝል እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ፡ በሰበካው ውስጥ የሚኖር፡ እያንዳንዱ ካህንና ምእመን፡ በዚህ ጉዳይ፡ በብርቱ አስቦበት፡ የየድርሻውን ተገቢ ግዳጅ እንዲፈጽም የሚያስፈልግ ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ በኩል ያለውን ኃላፊነት ይዞ፡ አግባብ የኾነውን፡ ማናቸውንም ጥናት እያደረገ፡ በሥራ ላይ ሊውል የሚችለውን ዕቅድ ማውጣትና መመሪያ መስጠት፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የምግባረ ሠናይና የማኅበራዊ አገልግሎት መምሪያ ተግባር ይኾናል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፩፡ ከዚህ በላይ፡ በዝርዝር የተገለጹት፡ የቤተ ክህነት አገልግሎቶችና ተግባሮች፡ መልካም ፍሬን ሊሰጡ የሚችሉት፡ አስተዳደሩ የተቃናና ድርጅቱም የተሟላ ሲኾን ነውና፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ በሰበካው አስተዳደር ደንብ ውስጥ እንደተመለከተው፡ በተሰጠው ሥልጣን፡ ለዚሁ ግብ የሚያበቃውን ግዳጁን መፈጸም ይኖርበታል፤ ይህም፡ እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል፡ ዝርዝሩ፡ በዚሁ ደንብ ውስጥ ተመልክቷል፡፡

ስለሰበካው አስተዳደርና ስለድርጅቱ መሟላት፡ አስፈላጊውን የውስጥ ደንብ ማውጣትና ተገቢውን መመሪያ መስጠት፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የአስተዳደርና የገንዘብ መምሪያ ተግባር ይኾናል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፮፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ በሚንቀሳቀስና በማይንቀሳቀስ፥ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት፥ በልዩ ልዩ መልክ፡ ሀብትና ንብረት ሊኖረው ስለሚችል፥ ይኸው ሀብትና ንብረት፡ በሰበካው አስተዳደር ደንብ፡ ፩ኛ አንቀጽ የተዘረዘረው ኾኖ፡ እርሱም፡ በትክክል ታውቆና ተመዝግቦ የሚጠበቅበትን፥ ከዚህ በላይ፡ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማስፈጸምም፡ በልማት ላይ የሚውልበትን ኹሉ ማድረግ፡ የሰበካው ጉባኤ አስተዳደር፡ ዋና ግዳጅ መኾኑ መታወቅ አለበት።

የሰበካው አስተዳደር፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን ቦታና መሬት፥ ሕንፃና ሌላም፡ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ኹሉ፡ በዝርዝር መዝግቦ ከያዘ በኋላ፡ ያ ንብረት፡ ሊለማና በጥቅም ላይ ሊውል ስለሚቻልበት ዘዴ፡ ተገቢው ጥናት እንዲደረግ፡ አሳቡን በጽሑፍ፡ ለቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የልማትና ንብረት መምሪያ፥ እንዲሁም፡ ለቤተ ክህነት፡ ልማት ባለአደራ (Commission) መሥሪያ ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል። ስለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት፥ ስለጥበቃውና ልማቱን ስለሚመለከተውም ጉዳይ ኹሉ፡ ከቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የልማትና ንብረት መምሪያ የሚተለለፍለትን የውስጥ ደንብና የሚሰጠውን መመሪያ ይከተላል።

ንዑስ አንቀጽ ፯፡ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ዓላማዎችና ተግባሮች በቀር፡ ሌሎች፡ በሰበካው ውስጥ፡ ቤተ ክህነትን የሚነኩ ጉዳዮች ቢኖሩ፡ የሰበካው ጉባኤ አስተዳደር እያየ፡ አስፈላጊውን ኹሉ፡ ባግባቡ ይፈጽማል። ከዓቅሙ በላይ የኾነ ጉዳይ ቢገጥመው፡ ያን ጉዳይ፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፥ በእርሱም አማካይነት፡ ለአውራጃው ሰበካ ጉባኤ ሊያቀርብ ይችላል።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሱት ዓላማዎችና ተግባሮች፡ በሥራ ላይ የሚውሉበት ዝርዝር ጥናትና ዕቅድ ኹሉ፡ ከንድፉ ጋር፡ በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ የጥናትና የሥራ ዕቅድ መምሪያ የሚዘጋጅ ስለኾነ፡ የሰበካው አስተዳደር፡ በዚህ ረገድ፡ የሚፈልገውን ለማግኘት፡ ከዚሁ መምሪያ መጠየቅ ይኖርበታል።

<u>ስለ፮ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ስለሰበካው ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር የሚዘረዝር ነው። በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት ሥልጣኖችና ተግባሮች፡ በ፫ኛው አንቀጽ፥ በ፩ኛው ንዑስ አንቀጽ እንደተመለከተው፡ በሰበካው አስተዳደር ደንብ መሠረት ለሚቋቋመው የአስተዳደር ጉባኤ የተሰጡ መኾናቸው መታወቅ ይኖርበታል።

ይህ የአስተዳደር ጉባኤ፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም ኾኖ፡-

ንዑስ አንቀጽ ፩. ከዚህ ቀደም ባለው፡ በ፩ኛው አንቀጽ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች፡ በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ፡ አስፈላጊ ኾኖ ሲያገኘው፡ ለምሳሌ፡ ትምህርትን በሚመለከት፡ ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ምልክና፥ ከመካናተ አእምሮና ከመሳሰሉት ልዩ ልዩ የትምህርት ተቅዋማት ጋር መተባበር ይችላል ማለት ነው። በዚህ ዓይነት፡ የምግባረ ሠናይንና የማኅበራዊ አገልግሎትን ጉዳዮች፡ ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት፥ ከማኅበራዊ ጉዳዮችና ከሕዝብ ጤና ጥበቃ ምልክናዎች፥ ከድኩማን መርጃ ድርጅት፥ ከከተማው ማዘጋጃ ቤትና ከመሳሰሉ፡ ልዩ ልዩ፡ የግልና የሕዝብ፥ የመንግሥትም ድርጅቶች ጋር፥ እንዲሁም፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ የቦታና የሕንፃ፥ የመሬትና የእርሻ፥ የገንዘብና የሌላ ሀብትና ንብረት፡ የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን ዘዴ፡ ከከተማው ማዘጋጃ ቤት፥ ከሕንፃ ሥራ፥ ከእርሻና ልማት ምልክናዎች፥ ከአብያተ ንዋይና ከልዩ ልዩ የልማት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

ንዑስ አንቀጽ ፪. በዚህ ንዑስ አንቀጽ፡-

በ(ሀ) ተራ ፊደል ስለተመለከተው ነገር፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ ተግባሩ፡ ምክር እያደረገ፡ ለአስተዳዳሪው፡ አስተያየት መስጠት ነው፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት፡ ጉዳዩ፡ መንፈሳዊነትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ስለኾነ፡ ይህን ስለመሳሰለው ኹሉ፡ ውሳኔ የመስጠቱ ሥልጣን፡ የብፁዓን ሊቃነ ካህናቱ ጉባኤ ብቻ በመኾኑ ነው፡፡ ስለንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት አጠባበቅም፡ በግንቦት ፩ ቀን፥ ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. ፩ኛ ዓመት፥ ቁጥር ፪ ቃለ አዋዲ በወጣው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት አጠባበቅ ድርጅት ደንብ መሠረት ይሠራል፡፡

በ(ለ) ተራ ፊደል ስለተጠቀሰው፡ ስለካህናት አስተዳደር፡ ማለትም፡ ስለሥራቸው መደብና ስለደመወዛቸው፡ ውሳኔ መስጠትና ይህንኑ፡ ለክፍሉ አውራጃ ቤተ ክህነት በማስታወቅ መሥራት ይቻላል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፫. የሰበካው አስተዳደር፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን የማይንቀሳቀስ ንብረት፡ ከ፭ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን ለማከራየትና የሌላውንም ንብረት ለመከራየት፥ ወይም፡ ይህንኑ፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን ንብረት አስይዞ፡ ገንዘብ ለመበደር፡ በክፍሉ ሀገረ ስብከት በኩል፡ ለቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት አስታውቆ፡ ሊያስፈቅድ እንደሚገባው፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ ያመለክታል፡፡ ይህ ፈቃድ ያስፈለገበት ምክንያት፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያ ሀብት የኾነው፡ ቦታ፥ ሕንፃና ርስት፡ ባልኾነ መንገድ፡ እንዳይባክንና ከጉዳት ላይ እንዳይወድቅ፡ በጥንቃቄ ለመጠበቅ ስለኾነ፡ ይህን የመሰለው አፈጻጸም፡ ትክክለኛውን ሥርዓት እንዲከተልና እንዲይዝ ለማድረግ ሲባል መኾኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ይህንኑ፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን የማይንቀሳቀስ ንብረት፡ ከ፭ ዓመታት በታች፡ ለምሳሌ፡ ለ፪፥ ወይም፡ ለ፬፥ ወይም፡ ለ፭ ዓመታትም ቢኾን፡ በክፍሉ ሀገረ ስብከት በኩል፡ ለቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት አስታውቆ፡ ማስፈቀድ ሳያስፈልገው፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ በራሱ ሥልጣን፡ ደንቡን ተከትሎ፡ ተገቢውን ጥናትና ምርምር፥ ምክክርም ካደረገ በኋላ፡ ሲወስን፡ የተባለውን ንብረት፡ ለማከራየት እና/ወይም፡ ለመከራየት ይችላል፡፡ ይህ አሠራር የተተለመው፡ ሥራውን ለማቀላጠፍ ጭምር ታስቦ ነው፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፬. በዚህ ንዑስ አንቀጽ፡-

በ(ሀ) ተራ ፊደል መሠረት፡ ውሉን የሚዋዋለውና በጽሑፍ ኪዳኑ የሚያጸናው፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ነው፡፡ ይኸውም ውል የሚፈጸመው፡ በቅድሚያ፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉባኤ፡ በሰበካው አስተዳደር ደንብ መሠረት መክሮ፡ ከተስማማበት በኋላ መኾኑን፡ ንዑስ አንቀጹ ያስገነዝባል፡፡

በ(ለ) ተራ ፊደል እንደተመለከተው፡ የመክሰስንና የመከሰስን ነገር፡ እንደጉዳዩ አሳሳቢነትና ከፍተኛነት፡ ከዳኝነት አስተዳደር ዘንድ፡ ራሱ ቀርቦ፥ ወይም፡ ምክትል ሊቀ መንበሩን፥ ወይም፡ የጽሕፈት ቤቱን ሹም በመወከል፥ ወይም፡ ችሎታ ያለውና የታመነ ነገረ ፈጅ በማቆም፡ ማስረዳት፥ መልስ መስጠትና መከራከር ያለበት፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይኾናል፤ አስተዳዳሪው፡ ይህንኑ ኹኔታ፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት አስታውቆ፡ እንዲተባበረው ማድረግም አለበት፡፡

በ(ሐ) ተራ ፊደል እንደተደነገገው፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ ስጦታዎችን በመቀበልም ኾነ፡ በሌላ ዘዴ፡ ገንዘብ የሚሰበሰበው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ባለው ሒሳብ ክፍልና ገንዘብ ተቀባይ አማካይነት ነው።

የተገኘውና የተሰበሰበው፡ ማናቸውም ገንዘብ፡ ባቅራቢያ ባለ፡ የታወቀ ሕጋዊ ቤተ ንዋይ ውስጥ፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም፡ ሒሳብ ተከፍቶ እንዲቀመጥ፡ ይኸው ንዑስ አንቀጽ ይጠይቃል።

ንዑስ አንቀጽ ፳. የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ ከከፍተኛዎቹ ተግባሮቹና ኃላፊነቶቹ መካከል፡ አንዱ፡ ዓይነተኛው፡ በየዓመቱ፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን፡ የገቢ ወጪ ድልድል (budget) መመርመር፥ መወሰንና መፍቀድ መኾኑን፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ ያመለክታል።

የአንድ ጥሩ ድርጅት፡ የሥራ ዕቅድና ውጤት የሚመዘነው፡ ባለው የተስተካከለ የገቢ ወጪ ድልድል ስለኾነ፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ዓላማና ተግባር፡ መልካም ፍሬን ሊያስገኝ የሚችል ይኾን ዘንድ፡ የመጀመሪያ ሥራው ሊያደርገው የሚገባው፡ የዓመቱን የገቢ ወጪ ድልድል፡ በቅድሚያ መርምሮ መወሰን ነው። የገቢ ወጪ ድልድል የሌለው ማናቸውም፡ የግል፥ የቤተሰብ፥ ወይም፡ የኅብረተሰብ ሥራ፡ ማሠሪያ የሌለው፡ የተበተነ ነዶ ማለት ስለኾነ፡ ይህ ግዳጅ መፈጸሙን፡ የሰበካው አስተዳዳሪና የአስተዳደሩ ጉባኤ፡ በጥብቅ አስበውበት ሊፈጽሙት ይገባል።

በዚህ የገቢ ወጪ ድልድል ውስጥ፡ የገቢው ዝርዝር፡ በአንድ ዓምድ፥ የወጪው ዝርዝር ደግሞ፡ በኹለተኛው ዓምድ ላይ ሠፍሮ፡ መመዛዘን አለበት። "ገቢ" የሚባለው፡ በሰበካው አስተዳደር ደንብ፡ በ፲፩ኛው አንቀጽ፡ በ፩ኛው ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘረው ሲኾን፥ "ወጪ" የሚባለው ደግሞ፡ "ለአስተዳዳሪውና ለካህናቱ፡ ማለትም፡ ለቀዳስያኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት፥ በማስተማርና በስብከት፥ በድብትርናም (በመዘምርነትም) ለሚያገለግሉት፥ እንዲሁም፡ ለጽሕፈት ቤቱ ሹምና ለሌሎቹ ሠራተኞች፡ የሚከፈለው ደመወዝ፥ በተጨማሪም፡ ከላይ የተዘረዘሩትን፡ ትምህርት ቤትን፥ በጎ ሥራዎችንና የመሳሰሉትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ለተቀጠሩ ሠራተኞች ደመወዝና የሥራ ማስኬጃዎች፥ ለአልባሳትና ንዋያት ቅድሳት፥ ለሕንፃዎች መጠገኛ፥ ለጽዳት መጠበቂያ፥ ለችግረኞች መርጃ፥ ለውኃ ዋጋ፥ ለመብራት ክፍያና ለስልክ ኪራይ፥ ለጽሕፈት አላቂ መሣሪያዎችና ቀዋሚ ዕቃዎች መግዣ" ተብሎ፡ ለመሳሰሉት አስፈላጊ ነገሮች ይደለደላል።

የገቢ ወጪ ድልድል የሚዘጋጀው፡ በገቢው መጠን፡ መጠባበቂያንና በተካባች የሚያዝ ሒሳብን ጨምሮ ስለኾነ፡ በዚህ ዓይነት፡ የገቢ ወጪ ድልድሉን፡ ቀደም ብሎ በጊዜውና በጥንቃቄ አዘጋጅቶ ማቅረብ ያለበት፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤቱ ሹም ነው። የየሰበካው ቤተክርስቲያን የገቢ ወጪ ድልድል፡ በትክክል የቀረበና የተፈቀደ፥ የሚሠራበትም መኾኑን፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፡ በቅርብ ኾኖ መርዳትና መቆጣጠር አለበት።

የአስተዳደሩ ጉባኤ፡ የቀረበለትን የገቢ ወጪ ድልድል ረቂቅ መርምሮ፡ በማሻሻልም ኾነ ባለማሻሻል፡ ከተስማማበት በኋላ፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል፤ የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትም፡ ድልድሉን፡ በፍጥነት አይቶ፡ ከአስተያየት ጋር፡ ለሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት በቶሎ መላክ፥ የሀገረ ስብከቱም ጽሕፈት ቤት፡ ያን አይቶ፡ በተላለፈለት መስመር በኩል፡ ሳያዘገይ፡ እንዲመልሰው ያስፈልጋል። ይህን የመሰለው አሠራር፡ ችግር እንዳይፈጥር፡ መቀላጠፍ ስላለበት፡ ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት በወጣ፡ እጅግ ቢበዛ፡ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡ ከሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ደርሶ፡ ተመልሶ፡ ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት መድረስ አለበት።

የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት፡ የዓመቱ ገቢ ወጪ ድልድል፡ በዚህ ኹኔታ ተፈጽሞ፡ በጊዜው ባይደርሰው፡ ይህንኑ በመግለጽና የድልድሉን ቅጂ በማያያዝ፡ ለቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፡ በጽሑፍ ማመልከትና አስቸኳይ መልስ ማግኘት ይችላል፡፡ የተላለፈው የገቢ ወጪ ድልድል፡ በዚህ መልክ ተፈቅዶ እስኪደርሰውም፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ ባለፈው ዓመት በተፈቀደለት ድልድል መሠረት፡ ሥራውን መቀጠል ስለሚችል፡ በተግባሩ እንቅስቃሴና በአገልግሎቱ ግዳጅ አፈጻጸም በኩል፡ ችግር እንዳይደርስ ማድርግ ያስፈልጋል፡፡

ንዑስ አንቀጽ ፮. በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በዓመት አንድ ጊዜ፡ ባለፈው ዓመት የተሠሩትንና ለሚቀጥለው ዓመት የታቀዱትን ሥራዎች፡ በዝርዝር የሚያመለክት ጽሑፍ መግለጫ እንዲቀርብለት ያስፈልጋል፡፡ የሚቀጥለው ዓመት የገቢ ወጪ ድልድል ከመፈቀዱ በፊት፡ የአስተዳደሩ ጉባኤ፡ ይህን መግለጫ መመርመር አለበት፡፡ ያለፈው ዓመት የገቢ ወጪ ድልድል፡ በትክክል የተሠራበት መኾን ያለመኾኑ፥ ለሚቀጥለውም ዓመት የሚያስፈልገው፡ የገቢ ወጪ ድልድል፡ ምን ያህልና ለምን ለምን እንደሚውል፡ በመግለጫው ውስጥ እንዲብራራ ያስፈልጋል፡፡ ይህን መግለጫ አዘጋጅቶ፡ ለአስተዳዳሪው ካሳየና ካስረዳ በኋላ፡ ለአስተዳደሩ ጉባኤ ማቅረብ ያለበት፡ የሰበካው ጽሕፈት ቤት ሹም ነው፡፡

<u>ስለ፯ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ የሰበካው ጉባኤ አቋም፡ እንዴት እንደኾነ፡ ባጭር ያሳያል፡፡ ቀደም ብሎ፡ በ፫ኛው አንቀጽ እንደተገለጸው፡ “የሰበካው ጉባኤ” የሚባለው፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የኾኑት ካህናት፥ እንዲሁም፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩት፡ የተመዘገቡት፡ ምእመናንና ምእመናት የሚገኙበት ጠቅላላው ጉባኤ ነው፡፡

ይህ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ፡ በማናቸውም ጊዜ፥ ነገር ግን፡ በዓመት እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ጊዜያት፡ በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ፡ ጠቅላላ ስብሰባ ማድረግ አለበት፡፡ የሚሰበሰበውም፡ የአስተዳደር ጉባኤ አባሎችን ለመምረጥ፥ በሰበካው ውስጥ የተፈጸሙትንና ለወደፊት የታቀዱትን ሥራዎች ለመግለጽ፥ እንዲሁም፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ በመላው ሊያውቁትና ሊነጋገሩበት የሚያስፈልግ፡ ማናቸውም ዓይነት ጉዳይ ቢኖር፡ ያን ለማቅረብ ነው፡፡ የሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ፡ በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፥ ወይም፡ በአስተዳደሩ ጉባኤ ሲወሰን፡ ሊጠራና ሊሰበሰብ ይቻላል፡፡

ለሰበካው ጉባኤ የአስተዳደር አወቃቀርና የሥራ አመራር አመች ይኾን ዘንድ፡-

ሀ. በሰበካው ጉባኤ ስም ኾኖ፡ ለሰበካው ጉባኤ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር የሚሠራ፡ ከካህናቱና ከምእመናኑ መካከል የተመረጡ፡ ቁጥራቸው የተወሰነ አባሎች የሚገኙበት የአስተዳደር ጉባኤ ይኖራል፡፡

ለ. በደንቡ የተመለከቱትን ተግባሮችና በአስተዳደሩ ጉባኤ የሚሰጡትን ውሳኔዎች የሚያስፈጽም፡ አንድ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይኖራል፡፡

ሐ. አስተዳዳሪውን በቅርብ የሚረዳና ጽሕፈት ቤቱን አቋቁሞ፡ በከፍተኛ ኃላፊነትና ትጋት የሚሠራ፡ አንድ የቤተ ክርስቲያኑ ጽሕፈት ቤት ሹም ይኖራል፡፡

መ. በክህነት፥ በማኅሌት፥ በትምህርት፥ በስብከት፥ በጽሕፈትና በሒሳብ ሙያ የሚያገለግሉ፥ በሌላም ተመሳሳይ ተግባር ተመድበው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ ደመወዝ እየተከፈላቸው የሚሠሩ ሠራተኞች ይኖራሉ፡፡

<u>ስለ፰ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ስለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አቋምና ስለአባሎቹ አመራረጥ ይዘረዝራል። ስለዚህ አንቀጽ በአጠቃላይ ለማብራራት፡ ከዚህ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ማመልከት አግባብ ይኾናል፡-

ሀ. "የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ" የሚባለው፡ ከበላይ ባለሥልጣን የሚሾመው፡ የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ሲኾን፡ እርሱም፡ የአስተዳደሩ ጉባኤ ሊቀ መንበር ነው፤

ለ. "የሰበካው ካህናት" የሚባሉት፡ በሰበካው ውስጥ፡ በቅዱስ ቍርባን በታተመ፡ ሕጋዊ ጋብቻ፥ ብሕትውና፥ ወይም፡ ምንኵስና ሥርዓት ከሚኖር፡ ከአንድ ካህን የሚፈለገውን፡ የማስተማር፥ የመጠበቅና የማገልገል ተግባር፡ አሟልተው ለመፈጸም የሚችሉ ኾነው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ በቅስና፥ በዲቁና፥ በድብትርና፥ በትምህርት፥ በስብከት፥ ይህንና ይህን በመሰለው፡ ከክህነትና ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የተያያዘ ሥራ ያላቸውን፡ ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም፡ ከቤተ ክህነት ደመወዝ የሚከፈላቸው አገልጋዮች ናቸው።

እንዲሁም፡ በሰበካው ክልል ውስጥ ባሉ፡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፥ የሕክምና ቤቶች፥ የመከላከያ ኃይል ሠፈሮች፥ ወህኒ ቤቶችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ውስጥ፡ በቤተ ክርስቲያን ስም ተቀጥረው፡ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ ካህናት ኹሉ፡ በዚህ የካህናት አንድነት የሚጠቃለሉ፥ በሰበካው አስተዳደርና አስተዳዳሪ ቁጥጥር ሥር ያሉ መኾናቸው፡ መታወቅ አለበት፤ እነዚህ ካህናት፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተመዘገቡና መታወቂያ ወረቀት ያላቸው እንዲኾኑ ያስፈልጋል።

እንግዴህ፡ እነዚህ ኹሉ ካህናት ተጠቃልለው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሊቀ መንበርነት ተሰብስበው፡ ቁጥራቸው፡ ከአሥር በላይ የኾነ እንደኾነ፡ ከመካከላቸው፡ አምስት፥ ወይም፡ ስድስት ካህናትን፡ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባልነት ይመርጣሉ፤ በዚህ መልክ የሚመረጡት፡ እኒህ ካህናት፡ በዕድሜ፥ በችሎታ፥ በመልካም አርአያነት፥ በምክርና በአሳብ አሰጣጥ፡ ተገቢና ብቁ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው፥ ሃይማኖታዊ ቅንዓትና መንፈሳዊ ንቃት ያላቸው ሊኾኑ ይገባል።

ሐ. "የሰበካው ምእመናን" የሚባሉት፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩትን፡ ወንዶችንና ሴቶችን፥ ሽማግሌዎችንና ወጣቶችንም የሚያጠቃልል ነው፤ የእነዚህ ምእመናን ቁጥር፡ እንደካህናቱ ኹሉ፡ በጣም አነስተኛ ከኾነ፡ በካህናቱ ወገን፡ በተመረጡት ልክ፡ ከእኒሁ ምእመናን መካከል፡ በሰበካው ጠቅላላ ጉባኤ፡ ኹለት፥ ወይም፡ ሦስት ምእመናን፡ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባልነት ይመረጣሉ፤ የምእመናኑ ቁጥር፡ በርካታ ከኾነ ግን፡ ያው፡ በካህናቱ ቁጥር ልክ፡ አምስት፥ ወይም፡ ስድስት ምእመናን ይመረጣሉ።

ከምእመናኑ መካከል የሚመረጡት አባሎች፡ በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟሉ፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም ሊኾኑ ይገባቸዋል፤ እነርሱም፡ የሰበካው አስተዳደር አመራር፥ ውጤቱም የተቃና ይኾን ዘንድ፡ ቁጥራቸው የተመዛዘነ ኾኖ፡ ከተለያየ የትምህርትና የኑሮ ደረጃ፥ የሥራና የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ ቢኾኑ ይመረጣል፤ ይጠቅማልም፤ ምክንያቱም፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ጾታ፥ ዕድሜ፥ የሥራ ኹኔታ፥ የትምህርትና የኑሮ ደረጃም ሳይወስናት፡ ኹሉን የያዘች፥ ኹሉም የሚገኙባት ስለኾነች፡ ኹሉን ለማገልገል የምትችለው፡ ኹሉም፡ በአስተዳደርዋና በሥራዋ ውስጥ ተሳታፊዎች ኾነው ሲገኙባት ስለኾነ ነው፡ "ከኹሉም ዓይነት ይመረጡ!" የሚያሰኘው።

የካህናቱም ኾነ የምእመናኑ ቁጥር፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ እጅግ ቢያንስ፡ ከኹለት ማነስ የለበትም፤ እጅግ ቢበዛም፡ ከስድስት መብለጥ የለበትም። ደግሞም፡ በማናቸውም ጊዜ፡ ለአስተዳደሩ ጉባኤ አባልነት የሚመረጡት ካህናትና ምእመናን፡ በኹለቱም ወገን፡ ቁጥራቸው፡ እኩል መኾን አለበት፤ ለምሳሌ፡ የተመረጡት ካህናት ቁጥር፡ ኹለት ከኾነ፡ የምእመናኑም ቁጥር፡ እንደዛው፡ ኹለት መኾን አለበት እንጂ፡ አራት ሊኾን አይችልም፤ ወይም፡ የካህናቱ ቁጥር፡ አራት ኾኖ፡ የምእመናኑ ቁጥር፡ እንደዛው፡ አራት መኾን አለበት እንጂ፡ ኹለት ሊኾን አይችልም፤ ምንጊዜም፡ የካህናቱም ኾነ፡ የምእመናኑ ቁጥር፡ እኩል መኾን አለበት።

በዚህ መልክ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት፡ ከምእመናኑ ወገን የተመረጡት፡ የአስተዳደሩ ጉባኤ አባሎች፡ ከላይ እንደተዘረዘረው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን እንዲከናወኑ የታቀዱትን ዓላማዎችና ተግባሮች ለማስፈጸም፡ እነሆ፡ በቤተ ክርስቲያን አቋምና አስተዳደር፥ አገልግሎትና ሀብት ውስጥ፡ በሥልጣን፥ በኃላፊነትና በሥራ፡ ሙሉ ተካፋዮች እንዲኾኑ ተደረገ ማለት ነው። ስለዚህ፡ ለምእመናን፡ በባለአደራነት የተሰጠው ይህ ሥልጣን፥ ኃላፊነትና ሥራ፡ ቀላል ባለመኾኑ፡ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባሎች እንዲኾኑ የተመረጡት ካህናትና ምእመናን፡ እነማን እንደኾኑ፡ መታወቅና መመዝገብ፥ ሹመታቸውም መጽደቅ ያለበት መኾኑ አያጠያይቅም።

ከዚህ የተነሣ፡ የምርጫው ውጤት የኾነውን የስም ዝርዝራቸውን፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፡ በሰበካ ጽሕፈት ቤቱ አማካይነት፡ ወዲያው፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ይልካል፤ የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትም፡ ያን አይቶ፡ በቶሎ፡ ለሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፤ የሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤትም፡ ይህንኑ አጽድቆ፡ ወደአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ከመለሰው በኋላ፡ የምርጫው ውጤት፡ በቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ታውቆ እንዲመዘገብ፡ ወደዚሁ፡ የመጨረሻ ባለሥልጣን ይልከዋል። የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፡ ከሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት፡ ጸድቆ የደረሰውን ምርጫ፡ ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት፡ በቶሎ መልሶ መላክ አለበት።

የሰበካው ጉባኤ፡ ጠቅላላ ስብሰባ አድርጎ፡ የአስተዳደሩን ጉባኤ አባሎች ስለሚመርጥበት ኹናቴ፥ ስለመራጩና ስለተመራጩ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ ውስጥ ተዘርዝሮ ተመልክቷል። ይኸውም ደንብ፡ በሥራ ላይ የሚውለው፡ እንደሚከተለው፡ በኹለት ደረጃ ነው፡-

፩ኛ፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩት መራጮችና ተመራጮች ካህናትና ምእመናን፡ በደንብ ተመዝግበው እስኪታወቁ፥ ለምዝገባውና ለመታወቂያው ወረቀት አሰጣጥ፡ የሚያስፈልጉት ዝግጅቶች እስኪደራጁም ድረስ፡ ከዚህ ቀጥለው የሚጠቀሱት ተግባሮች እንዲፈጸሙ ያስፈልጋል፤ ይኸውም፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ መሠረት፡ ቀደም ብለው የተገለጹትን፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩትን፥ እንዲሁም፡ ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉትን ካህናትና ምእመናን ለመመዝገብና መታወቂያ ለመስጠት፥ በጠቅላላ፡ አስፈላጊውን ድርጅት ኹሉ ለማቋቋምና ለማሟላት፡ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የሚረዳ፡ የሰበካውን አስተዳደር ጊዜያዊ ጉባኤ፡ በቅድሚያ መርጦ ሥራውን መጀመር ነው።

ይህንም ለማድረግ፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ በካህናቱ አማካይነት፥ እንዲሁም፡ በቤተ ክርስቲያኑ፡ በሰንበትና በበዓል ለሚገኘው ሕዝብ፡ ቀደም ብሎ በማስታወቅ፡ በሰበካው ውስጥ የሚኖሩት ምእመናን ኹሉ፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ እንዲሰበሰቡለት፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ከኹለት ሳምንታት በፊት፡ ጥሪ ያደርጋል።

በዚህ ስብሰባ ላይ፡ በተለይ የታወቁ ምእመናንና ምእመናት፥ በመንግሥትና በሕዝብ የኃላፊነት ሥራ ላይ የሚገኙ ታላላቅ ሰዎች፥ የዕድር፥ የሰንበቴና የልዩ ልዩ ማኅበሮች ሙሴዎች፥ በጠቅላላ፡ ገና ያልተመዘገቡም ቢኾኑ፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና በካህናቱ ዘንድ "የታወቁ ናቸው!" የተባሉ፡ የሰበካው ነዋሪዎች የኾኑት ምእመናን፡ በተቻለ መጠን እንዲገኙ እንጂ እንዳይቀሩ ተደርጎ መጠራት ይኖርባቸዋል።

በዚህ መልክ በሚጠራው ስብሰባ ላይ፡ ዓቅም ከፈቀደ፡ በቃለ ዓዋዲ የወጣው፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብና ይህ፡ የአፈጻጸሙ መምሪያ ለስብሰባው ተካፋዮች ይታደላል፤ አለዚያ፡ በንባብ ይሰማል። በዚህ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ፡ ስለደንቡ ለማብራራትና ለማስረዳት፡ በቤተ ክህነት የልማት ባለአደራ ድርጅት ሥር፡ ቀደም ብለው ከሠለጠኑት፡ ከአውራጃው ቤተ ክህነት ምሩቃን መካከል፡ አንዱ፡ መገኘት ይኖርበታል።

በስብሰባው ላይ የተገኙት፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ ደንቡን፡ በትክክል እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ፡ ቢቻል፡ በዚያው ስብሰባ ላይ፥ ባይቻል ግን፡ በሚቀጥለው ዕለተ ሰንበት፡ ይኸው ጠቅላላ ጉባኤ ተሰብስቦ፡ ከምእመናኑ መካከል፡ ቁጥራቸው፡ በደንቡ ውስጥ እንደተመለከተው፡ እንደሕዝቡ ብዛት፡ ከኹለት ያላነሰ፥ ከስድስት ያልበለጠ፥ ከወንዶችም፥ ከሴቶችም መካከል ይመረጣሉ።

ይህንም ምርጫ ለማስፈጸም፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ ቁጥራቸው፡ ከአምስት ያልበለጠ አባሎች የሚገኙበትን ጊዜያዊ ሕዋስ፡ ቀደም አድርጎ ያቋቁማል፤ የዚህ ሕዋስ አባሎች፡ ለዚህ ባለአደራነት ከሚበቁ ካህናትና ምእመናን መካከል ሊመረጡ ይቻላል። በዚሁ፡ በጊዜያዊነት ለሚቋቋመው፡ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ፡ ከካህናቱ በኩል የሚመረጡት አባሎች፡ በምእመናኑ ቁጥር ልክ፡ ቀደም ብሎ፥ ወይም፡ በዚያኑ ዕለት፥ ወይም፡ ከዚያ በኋላ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ በካህናቱ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ይመረጣሉ።

የእነዚህ የኹለቱም ጠቅላላ ስብሰባዎች፡ ማለትም፡ የካህናቱም ኾነ፡ የምእመናኑ ጉባኤዎች ሊቀ መንበር፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ነው። በዚህ ዓይነት፡ ከካህናቱና ከምእመናኑ መካከል የተመረጡት አባሎች፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉባኤ አባሎች ኾነው፡ ደንቡን ተከትለው፡ ለአስተዳደሩ ጉባኤ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር፡ ሥራቸውን ይቀጥላሉ። የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት፡ በቅድሚያ፡ በሚገባ ከተቋቋመ በኋላ፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩት፡ የካህናቱና የምእመናኑ መመዝገብና መታወቂያ ማግኘት፥ ሌላውም፡ ማናቸውም የሰበካው፡ የአስተዳደር አቋምና የሥራ አመራር፡ በደንቡ መሠረት፡ እስኪሟላና ሥርዓት ይዞ እስኪካኼድ ድረስ፡ በዚሁ ኃላፊነታቸው ይቆያሉ።

የዚህ፡ የጊዜያዊው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ግዳጅ፡ ቢቻል፡ በአንድ ዓመት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፤ ይህን ማድረግ የማይቻልበት፡ በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ግን፡ የአስተዳደሩ ጉባኤ የሥራ ዘመን፡ እስከኹለት ዓመታት ሊራዘም ይቻላል፤ ከዚያ በላይ ግን ሊኾን አይቻልም።

፪ኛ፡ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚኖሩት ካህናትና ምእመናን፡ ተመዝግበውና መታወቂያ አግኝተው እንዳበቁ፡ መደበኛውን የአስተዳደር ጉባኤ ለመምረጥ፡ የሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ ይጠራል። የዚህ ጠቅላላ ስብሰባ መደረጊያ ቀን፡ በጊዜያዊው የአስተዳደር ጉባኤ፡ ከአንድ ወር ቀደም ብሎ፡ ከተወሰነ በኋላ፡ በአስተዳዳሪው፥ በካህናቱና በሰበካው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አማካይነት፡ በሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ሊገኙ ለሚገባቸው፡ ለተመዘገቡት ካህናትና ምእመናን፡ በቃልና በጽሕፈት፡ ጥሪ ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

ከተመዘገቡት ካህናትና ምእመናን መካከል፡ አብዛኛዎቹ፡ በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ከተገኙ፡ የካህናቱንም ኾነ፡ የምእመናኑን ምርጫ፡ ከላይ እንደተዘረዘረው፡ በደንቡ መሠረት፡ መፈጸም ይቻላል፡፡ ምርጫውን ለመፈጸም፡ በሰበካ ነዋሪነታቸው፡ ከተሰበሰቡት ካህናትና ምእመናን መካከል፡ ከቀናት በፊት፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና በጽሕፈት ቤቱ ሹም ተመልምለው የቀረቡት፡ የአስመራጩ ሕዋስ አባሎች፡ ስማቸው፡ በቅድሚያ፡ ለጠቅላላው ጉባኤ ተገልጾ፡ በአንድ ድምፅ ይሠየማሉ፡፡

በእነርሱም አማካይነት፡ በመጀመሪያ፡ ከዚያው፡ ከጠቅላላው ጉባኤ መካከል፡ በዚያው፡ በጠቅላላው ጉባኤ፡ የእጩዎች ስም ዝርዝር ተዘጋጅቶ፡ ለዚያው፡ ለጠቅላላው ጉባኤ ይቀርባል፡፡ ጠቅላላው ጉባኤ በሚወስነው መሠረት፡ በእጩነት ከቀረቡት ብቁዎች መካከል፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ በጽሕፈት፥ ወይም፡ እጅ በማንሣት፡ የአስተዳደሩን ጉባኤ አባሎች ይመርጣሉ፡፡

በዚህ ሥርዓት የተከናወነው የድምፅ አሰጣጡ ውጤት ተቆጥሮ በተገኘው ብልጫ፡ ምርጫው ይፈጸማል፤ ይኸውም፡ በቅድሚያ፡ ኹሉም እጩዎች ያገኙት የድምፅ ቁጥር ከተመዘገበ በኋላ፡ በከፍተኛ ቁጥር ከተመረጠው ጀምሮ፡ የቀሩት፡ እንደቅደም ተከተል ተራቸው ወደታች፡ ስማቸው ተዘርዝሮ ይጻፍና፡ አብላጫ ድምፅ ያገኙት እንደተመረጡ የሚቆጠርበት ሥርዓት ነው፡፡ የምርጫው ድምፅ ውጤትም፡ ወዲያውኑ፡ ለጠቅላላው ጉባኤ ይገለጻል፡፡ በሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ውስጥ፡ ወደፊት፡ ክፍት የሚኾን፡ የአባል ሥፍራ በተገኘ ጊዜ፡ በደንቡ መሠረት መተካት ስለሚያስፈልግ፡ ይኸው የምርጫው ድምፅ ውጤት፡ የአስመራጩ ሕዋስ አባሎች፡ ጽሑፍ ኪዳናቸውን አሥፍረውበት፡ በሰበካው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይቀመጣል፡፡

ይህን ምርጫ ለማስፈጸም፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ሹም ኃላፊነት፡ ቁጥራቸው፡ ከአምስት ያልበለጠ፥ ከካህናቱና ከምእመናኑ መካከል፥ ከእያንዳንዱ ሠፈር፥ ለዚህ አደራና ኃላፊነት ብቁ የኾኑትን፡ የምርጫ አስፈጻሚ ሕዋስ አባሎች ይመርጣል፤ ምርጫውም ለሰበካው ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፤ ምናልባት፡ ከጠቅላላው ጉባኤ ሙሉ ድጋፍ ያላገኘ እጩ ቢኖር፡ በጠቅላላው ጉባኤ እንዲተካ ማድረግ አግባብ ይኾናል፡፡ እነዚህ የምርጫ አስፈጻሚው ሕዋስ አባሎች፡ ከሰበካው ጽሕፈት ቤት ሹም ጋር ኾነው፡ ምርጫው በትክክል የተፈጸመ መኾኑን ያረጋግጣሉ፡፡

<u>ስለ፱ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ስለአስተዳዳሪው ሥልጣን፥ ኃላፊነትና ተግባር በዝርዝር የሚያስረዳ ነው፡፡

"አስተዳዳሪ" የሚባለው፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አለቃ፥ ሥራ አስኪያጅና ፈጻሚ፥ የሰበካው ሊቀ ካህናት፥ የሰበካው ጠቅላላ ጉባኤና አስተዳደር ጉባኤ ሊቀመንበር እንደመኾኑ፡ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት የተጣለበት ስለኾነ፡ በታላቅ ትጋት፥ ንቃትና ችሎታ የሚሠራ መኾን አለበት፡፡ ለሰበካው ካህናትና ምእመናን፥ በጠቅላላውም፡ ለቤተ ክርስቲያን ዓላማ አፈጻጸምና ለልማት ዕድገት፡ "ይጠቅማል!" ተብሎ የወጣው የሰበካ አስተዳደር ደንብና ሌሎቹም ደንቦች ኹሉ፡ ፍሬ ሊሰጡ የሚችሉት፡ በአስተዳዳሪው ብርታትና ጥረት ስለኾነ፡ የቃለ ዓዋዲው ደንብ፡ ሥራ ላይ የመዋሉና የተፈለገውን ውጤት የመስጠቱ መጠን የሚለካው፡ እንደአስተዳዳሪው ዓይነት መኾኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

የአስተዳዳሪው ኃላፊነትና ተግባር፥ ከእርሱ የሚጠበቀውም የሥራ ፍሬ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ ውስጥ በዝርዝር እንደተመለከተው፥ በዚህ ማብራሪያም፡ በየቦታው እንደተገለጸው፡ ይህን ያህል፡ ከባድና አያሌ ከኾነ፥ አኹን፡ በቦታው ተመድቦ ያለው፥ ከሌለም፡ ወደፊት የሚመደበው፡ ይኸው የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፡ ይህንኑ የተጣለበትን ግዳጅ፡ በትክክል መፈጸም የሚችል፥ ወይም፡ የማይችል መኾኑን አጣርቶ ማረጋገጥ፥ ችሎታው የሚያንሰው ከኾነም፡ እንዲሚላለት የሚደረግበትን መንገድ ማደራጀት፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት የኃላፊነት ድርሻ ይኾናል፤ ከዚህ የተነሣ፡ ይህ ጉዳይ፡ በመጨረሻው ባለሥልጣን ዘንድ፡ በብርቱ ሊታሰብበት የሚገባ፡ ከፍተኛና አሳሳቢ ቍም ነገር መኾኑ፡ ግልጽ ነው።

በሰበካው ቤተ ክርስቲያን በኵል ስለሚደርሰው፡ ስለማናቸውም ኹኔታ፡ ተጠያቂው፡ አስተዳዳሪው መኾኑ መታወቅ አለበት። ሕግ፥ ወይም፡ ደንብ፡ ፈጻሚና አስፈጻሚ ከሌለው፡ መታወጁ ብቻ በቂ ሊኾን አይችልም። ከዚህ የተነሣ፡ ለሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ መተዳደሪያና መመሪያ እንዲኾን፡ በቃለ ዓዋዲ የወጣውን፡ የሰበካ ጉባኤ ደንብ ለማስፈጸም፡ ዋናው ዓይነተኛ አደራና ኃላፊነት የተጣለው፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ላይ ስለኾነ፡ እያንዳንዱ፡ ለዚህ እልቅና የበቃው ተሿሚ፡ ይህን ግዳጅ ለመፈጸም የተዘጋጀና በቆራጥነት የተነሣ፡ "መልካም አገልጋይ" መኾን አለበት። ነገር ግን፡ ይህን ግዳጁን፡ በትክክልና በአግባቡ ለማካኼድ፥ ለማከናወንም የማይችል፥ ወይም፡ ፈቃደኛነትና ትጋት የሌለው ከኾነ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፡ እየተከታተለ፡ ተገቢውን ጥብቅ የአስተዳደር ብያኔ እየሰጠ፡ ይኸው በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ፡ ቀዳሚ ግዳጁ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

<u>ስለ፲ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ስለሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ የጽሕፈት ቤት ሹም፡ ሥራና ኃላፊነት ዘርዝሮ ያስረዳል።

ማናቸውም ዓላማና ተግባር፡ በሥራ ላይ ውሎ፡ ከግብ ሊደርስ የሚችለው፡ መሣሪያና ፈጻሚ የኾነ ሠራተኛ ሲኖረው ነው። የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መምሪያና የአስተዳደሩ ጉባኤ ውሳኔ፥ ከበላይ የሚደርሰው ትእዛዝና በዚሁ ደንብ መሠረት ሊፈጸም የሚገባው ተግባር ኹሉ፡ ውጤት የሚኖረው፡ በጽሕፈት ተይዞ፡ ባግባቡ፡ ለሚመለከተው ክፍል፡ በጊዜው ተላልፎ፡ እንዲደርስና እንዲፈጸም ሲደረግ ብቻ ነው። በጠቅላላ፡ በሰበካው ጉባኤ አስተዳደር ደንብ ውስጥ የተመለከተው ሥራ፡ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ፡ ጠንካራና ትጉህ፥ ንቁና ታማኝ፥ ታዛዥና ግብረ ገብ የኾነ፥ ሙያውና ችሎታው ያለው፡ ጥሩ ጸሓፊ እንዲኖር ያስፈልጋል። ስለዚህ፡ ይህ፡ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ደንብ፡ ጠንካራ መሠረት ይዞ እንዲቋቋምና ሥራው፡ በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን መመሪያዎች ተከትሎ እንዲካኼድ፡ በቅድሚያ እንዲኖር የሚያስፈልገው፡ በእርግጥ፡ የጽሕፈት ቤት ሹም ነው።

ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ የቀኝ ክንድ ኾኖ፡ አስተዳዳሪውን የሚረዳው፡ ይኸው፡ የጽሕፈት ቤት ሹም ስለኾነ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ተመርጦ፡ ሥራውን እስኪጀምርና ይኸው ጉባኤ፡ የጽሕፈት ቤቱን ሹም እስኪሠይም ድረስ፡ አስተዳዳሪው፡ በቅድሚያ፡ በደንቡ ውስጥ በተመለከተው አንቀጽ ያለውን ተግባርና ኃላፊነት፡ "ሊፈጽም ይችላል!" ብሎ፡ እምነት የሚጥልበትን፡ አንድ የጽሕፈት ቤት ሹም፡ ከካህናቱ፥ ወይም፡ ከምእመናኑ መካከል፡ በጊዜያዊነት መድቦ ሊያሠራ ይችላል።

በዚህ ዓይነት ተሠይሞ ሲሠራ የቆየው ግለሰብ፡ በአገልግሎቱና በውጤቱ፡ ተስማሚና ብቁ ኾኖ ከተገኘ፡ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ከተቋቋመ በኋላ፡ ሹመቱ፡ በዚሁ ጉባኤ ሊጸድቅለትና ሥራውን ሊቀጥል ይችላል፡፡

ይህን በመሰለ ይዞታ ተመልምሎ የሚመደበው፡ የሰበካው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሹም፡ የተሰጠው ተግባርና የተጣለበት ኃላፊነት፡ ከባድና ብርቱ ስለኾነ፥ አመራረጡ፡ በይበልጥ፡ ለሥራው በማሰብ፡ የቱን ያህል፡ ጥንቃቄ ሊደረግበት፥ እርሱም፡ ይህንኑ፡ በትክክል የተረዳ መኾኑ ሊረጋገጥ  እንደሚገባ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

<u>ስለ፲፩ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ "የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ንብረት" የሚባለው ምን እንደኾነ፥ ይኸስ ገንዘብና ንብረት፡ እንዴት ሊሰበሰብ፥ ሊጠበቅና በጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ዘርዝሮ የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህም፡ እንደሚከተለው፡ በይበልጥ ተብራርቷል፡፡

ሀ. ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን፡ "የመጀመሪያው ገቢ ነው!" ተብሎ የተጠቀሰው ገንዘብ፡ በሰበካው ክልል ውስጥ ከሚኖሩ፡ ከተመዘገቡትና ዓቅም ካላቸው ምእመናን፡ በወር፥ ወይም፡ በዓመት የሚከፈል ሒሳብ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው፡ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሀብት፡ ወደግሉ ከማከማቸቱ፥ ወደቤቱም ከማግባቱ በፊት፡ አሥራት እያወጣ፡ በቅድሚያ፡ ለፈጣሪው፡ በረከትን ማቅረብ፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ መካከለኛው እርከን ከኾነው፡ ከኪዳነ ኦሪቱ ጋር ተያይዞ የመጣልን ሥርዓት ኾኖ፡ ስንፈጽመው ኖረናል፤ ይህም የኾነው፡ "እንኳን ሥጋዊው ሀብታችን፡ እኛስ ራሳችን፡ የአምላካችን ንብረት አይደለንምን?" ወደሚለው፡ ወደመጀመሪያው፡ የኪዳነ ልቦና ሃይማኖታችን እስከተመለስንበትና ዛሬ እየኖርንበት እስከምንገኘው፡ እስከመጨረሻው ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ድረስ ማለት ነው፡፡

ይህን ሃይማኖታችንን መሠረት በማድረግ፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል፡ ካህኑ፡ ራሱን፡ ለአገልግሎት በመስጠት፥ ምእመኑም፡ እግዚአብሔር በለገሠው፡ የአካል ጉልበቱ፥ ወጥቶ ወርዶ፡ በወዙና በድካሙ ካፈራው ሲሳይ ከፍሎ በማበርከት፥ ወይም፡ የአእምሮ እውቀቱና የመንፈስ ብቅዓቱ ከሚያስገኙለት ልዩ ሀብት፡ የበኩሉን አስተዋጽዖ ተሳትፎ በማድረግ፡ በየሰበካው ያለውን ቤተ ክርስቲያን መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ ደንብ፡ ካህናትም፥ ምእመናንም፡ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና አመራር፥ ሀብትና ሥልጣን፡ ሙሉ ተካፋዮች እንዲኾኑ የተደረገው፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ቤተ ክርስቲያን፡ የራሳቸው፥ በራሳቸውና ለራሳቸው ስለኾነች ነው፡፡ እንዲህ ከኾነም፡ የራሳቸው የኾነችውን ቤተ ክርስቲያናቸውን፡ እንደየዓቅማቸው መርዳትና መጠበቅ፥ መንከባከብም፡ የሃይማኖት ግዴታቸው መኾኑን ሊገነዘቡት ይገባል፤ ማናቸውም ሰው፡ የራሱ የኾነውን ቤት፡ ካልረዳና ካልደገፈ፥ ካልተንከባከበም፡ ሌላ፡ ማንም፡ ሊረዳውና ሊደግፈው፥ ሊንከባከብለትም የሚመጣ ከቶ ሊኖር አይችልም፡፡

በአገራችን፡ ቤተ ክርስርቲያን፡ እስካኹን፡ በሥጋዊው ረገድ፡ ስትደገፍ የኖረችው፡ እንደሥርዓታችን፡ በይበልጥ በመንግሥት ሲኾን፡ በተጨማሪ፡ የዚሁ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከኾኑት፡ ከአጼው ጀምሮ፡ በቤተ ሕዝቡና በቤተ ምልክናው ውስጥ የሚገኙትን፡ መሳፍንቱን፥ መኳንንቱንና ወይዛዝሩን ጭምር ይዞ፡ እስከተራው ግለሰብ ድረስ፡ እያንዳንዱ በጎ አድራጊ፡ ለእያንዳንዱ ቤተ መቅደስ፡ በሕይወቱ ሣለ፡ በሚሰጠው፥ በሚሞትበትም ጊዜ በኑዛዜ፡ በሚያወርሰው ቦታና ቤት፥ መሬትና ገንዘብ፥ ሌላም ልዩ ልዩ  ሀብት እንደነበረ፡ በይፋ ይታወቃል።

ከዚህ ጋር፡ መንግሥት፡ በዚሁ በቤተ ክህነት ቦታና መሬት፥ ሌላም ሀብት ላይ ጥሎ የሚሰበሰበውን የገቢ ግብር፡ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ ይኾን ዘንድ የሚፈቅደው፡ ይገኛል።

ዛሬ ግን፡ ጥንት፡ ማለትም፡ ከመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን አንሥቶና መካከለኛውን ዘመን አልፎ፡ እስከመጨረሻው ዘመን የዘለቀው፡ መንግሥታዊ ሥርዓታችን እየተቃወሰና እየተናጋ የመኼዱ ምልክት፡ ጎልቶ በመታየቱ፡ ይህንኑ ሥርዓታችንን፡ ከዚህ ጠንቀኛ አዝማሚያ ለማዳን፡ ይህን የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ፡ በቃለ ዓዋዲ አውጥቶ፡ በተግባር ላይ እንዲውል፡ ከማድረግ በቀር፡ ሌላ አማራጭ እንደማይኖር ተረጋገጠ። በዚህ ደንብ ላይ ተዘርዝሮ እንደተገለጸው፡ እንኳንስ፡ በዚህ አሳሳቢና አደገኛ የመሸጋገሪያ ድልድይ ላይ እየተጓዘች የምትገኘው፡ ጠቅላላዋ ቤተ ክህነት ትቅርና፡ እያንዳንዱ፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን ህልውናውና አገልግሎቱ ሊቀጥል፥ ዘመኑ ያስከተለውን፡ ውስብስብና ሰፊ የኾነ ዓላማውንና ተግባሩንም፡ ለመፈጸም፡ የቱን ያህል ከባድ እንደኾነ ለመገመት፡ ለማንም አያዳግትም።

እንግዴህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በእንደዚህ ያለ ኹኔታ ላይ የምትገኘው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ለዘመኑ ቤተ ሕዝቧ፡ ልታበረክት ለሚገባት ግዳጇ፡ "ገንዘብ ያስፈልጋታል!" የሚያሰኘው፡ ይህ እውነታ ነው። እንዲህ በሚባልበት ጊዜም፡ "ያ ገንዘብ የሚውለው ለማነው? ለምንስ ዓላማ ነው?" ከሚሉት ጥያቄዎች ጋር በማያያዝ፡ "በደንቡ ውስጥ የተመለከቱት ዓላማዎች፡ ለማን የሚጠቅሙ ናቸው? ለማንስ ደኅንነት ተብለው፡ የሚደረጉ ናቸው?" የሚሉትንም፡ አከታትሎ ማቅረብ ይገባል።

የጥያቄዎቹ መልስ፡ የኹሉም፡ ያው፡ "ለምእመናኑ ነው!" የሚል ይኾናል። አዎን! ጸሎቱ፥ መንፈሳዊ አገልግሎቱ፥ ትምህርት ቤቱ፥ ስብከተ ወንጌሉ፥ በጎው ሥራና ማኅበራዊ አገልግሎቱ፥ ሌላውም ተግባር ኹሉ፡ ያው ለሰበካው ቤተ ሕዝብ ነው።

ካህናቱም፡ ማለትም፡ ቀዳስያኑ፥ መዘምራኑ፥ መምህራኑ፥ ሰባክያኑ፥ ሌሎቹም፡ መላው፡ የቤተ ክህነትና የየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ኹሉ፥ የየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ሕንፃና ሌላውም ድርጅት ጭምር፡ አገልግሎታቸው፡ ያው፡ በየሰበካው ለሚኖሩትና የቤተ ሕዝቡ አባሎች ለኾኑት ምእመናንና ምእመናት መኾኑ፡ ለማንም የተሠወረ አይደለም።

ስለዚህ፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ሠራተኞች፥ ሕንፃውና ድርጅቶቹ ኹሉ፡ አገልግሎታቸው፡ ለዚያው፡ ለሰበካው ሕዝበ ክርስቲያን ከኾነ፡ የዚያው ሰበካ ሕዝበ ክርስቲያን ደግሞ፡ አስፈላጊውን አገልግሎት መልሳ ለምትሰጠው፡ ለዚችው የሰበካ ቤተ ክርስቲያኑ፡ አገልግሎት መስጠት የሚያስችላትን ዓቅም እንድታገኝ፡ መደገፍና መርዳት ይገባዋል። ይህን ምግባር መፈጸም የሚቻለውም፡ እያንዳንዱ ምእመን፡ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ ከሰጠው ሀብት፥ ከሚያገኘውም ገቢ፡ በፈቃዱ ከፍሎ ሲሰጥ ብቻ ነው። ይህ የምእመናን ስጦታ፡ በገንዘብ ብቻ ተተምኖ የሚቀርብ አይደለም፤ ገንዘብ የሌላቸው፡ ካህናትና ምእመናን፡ የጉልበት፥ የእውቀትና የሙያ፥ የአሳብና የምክር አስተዋጽዖዋችውን በማበርከት መሳተፍ ይችላሉ።

ይህን የመሰለው፡ የምእመናን አስተዋጽዖ፡ በዓለም ላይ ደርጅተውና ተስፋፍተው በሚገኙ፡ በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ፡ መሠረታዊ ተግባር ኾኖ ይሠራበታል።

እነዚህ፡ ዛሬ፡ የየራሳቸውን ፍላጎት አሟልተው፡ መልእክተኞቻቸውን፡ በየአህጉሩ÷ በእኛ አገር ጭምር በመላክ፡ በመላው ዓለም ተሠራጭተው የሚታዩት፡ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት ተቋማት፡ ይህን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስና ለሌሎችም ሕዝቦች ሊተርፉ የቻሉት፡ በየሰበካቸው ከሚኖሩት አባሎቻቸው የሚሰበስቡት፡ የአሥራትና የእርዳታ አስተዋጽዖ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት አካል የኾነውና በየሰበካው የሚኖረው፡ የምእመናን ቤተ ሕዝብም፡ ይህን ግዳጅ መፈጸም የሚያዳግተው ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

እንግዴህ፡ የተመዘገቡና ችሎታ ያላቸው ምእመናንና ምእመናት፡ በየሰበካቸው ቤተ ክርስቲያን፡ ሊከፍሉ የሚገባቸው፡ የገንዘብ አስተዋጽዖ ልክ፡ በዚያ፡ በሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ሊወሰን ይቻላል፡፡ ይኸም፡ በቅድሚያ፡ በሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ላይ ተጠንቶና ተመክሮበት፡ ከስምምነት ሲደረስበት፡ የሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ፡ እንዲያውቀውና እንዲያጸድቀው ይቀርብለታል፡፡

የአስተዋጽዖው ገንዘብ ልክ፡ በሦስት ደረጃ ተከፋፍሎ፡ ሊመደብና ሊወሰን ይችላል፤ ይኸውም፡ "ዝቅተኛ"÷ "መካከለኛ" እና "ከፍተኛ ገቢ ላላቸው ምእመናንና ምእመናት" ተብሎ ማለት ነው፡፡ ይህም ሒሳብ፡ በወር÷ ወይም፡ ተጠቃልሎ፡ በዓመት እንዲከፈል ማድረግ ይቻላል፤

ለምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው፡ | በወር፡ ፳፭ ቤሳ÷ | በዓመት፡ ፫ ብር፤ |
| መካከለኛ" " | " ፶ " | " ፮ " |
| ከፍተኛ " " | " ፩ ብር÷ | " ፲፪ " |

ወይም፡ በሌላ ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው፡ | በወር፡ ፩ ብር÷ | በዓመት፡ ፲፪ ብር፤ |
| መካከለኛ" " | " ፫ " | " ፴፮ " |
| ከፍተኛ " " | " ፭ " | " ፷ " |

እንደማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ፡ የዚህ የአስተዋጽዖው ገንዘብ አከፋፈል ጉዳይ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት፡ በሰበካ÷ በአውራጃና በሀገረ ስብከት ጉባኤዎች፡ በየደረጃው ተጠንቶና ተመክሮበት ካበቃ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ ለጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ቀርቦ ሲጸድቅ፡ የሚወሰን ይኾናል፤ እስከዚያውም፡ ከዚህ በላይ በተገለጸው ኹኔታ፡ ሲሠራበት ይቆያል፡፡

ይህ ጉዳይ፡ ምንም እንኳ፡ በዚህ ዓይነት የሚፈጸም ይኹን እንጂ፡ በእያንዳንዱ ምእመን፡ ፍጹም ሃይማኖታዊ ፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ ሊኾን እንደሚገባ፡ በግልጽ መታወቅና መነገር ያለበት ዓቢይ ቍም ነገር ነው፤ ስለዚህ፡ ማናቸውም ምእመን፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ፍቅር ሲል፡ እንዲህ፡ በስምምነት ከሚወሰነው በላይ፡ "እከፍላለሁ!" ካለ÷ ደግሞ፡ ከገቢውና ከደመወዙ÷ ወይም፡ ካለው ሀብት ላይ፡ አሥራት አውጥቶ ለመስጠት ፈቃደኛ ከኾነም፡ አይከለከልም፡፡

የአስተዋጽዖ ሒሳብ አከፋፈል፡ በገንዘብ ብቻ ሳይኾን፡ በሌላም ዓይነት ሊከፈል ይችላል፤ ይኸውም፡ እያንዳንዱ ምእመን፡ በገቢው ዓይነትና መጠን፡ መክፈል ይፈልግ ይኾናል።

ለምሳሌ:- ገበሬው: ከእህሉ፥ ነጋዴው: ከሸቀጡ፥ ሠራተኛው: ከደመወዙ፥ ይህ ኹሉ የሌለውም: ከሙያውና ከእውቀቱ፥ ከአእምሮውና ከጉልበቱ: አሥራት: በኵራት፥ ወይም: በዓቅሙ መጠን: ከፍሎና አውጥቶ መስጠት ይቀልለው ይኾናል፤ ይኸንንም: እንደፍላጎቱና እንደተገቢነቱ: መቀበል ይቻላል::

ለ. ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ቦታዎች፥ መሬቶችና ሕንፃዎች ኪራይና ሰብል፥ እንዲሁም: በስእለትና በልዩ ልዩ መልክ የሚገኘው ገቢ: በደንቡ መሠረት: በትክክል ከተሰበሰበና ከተጠበቀ: ብዙ ሥራ ሊያሠራ ስለሚችል: በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ግዳጃቸውን ስለመፈጸማቸው: የሰበካው አስተዳዳሪ፥ የአስተዳደሩ ጉባኤና የጽሕፈት ቤቱ ሹም: በብርቱ ሊያስቡበት የሚገባ የየድርሻቸው ኃላፊነት ነው::

ከዚህ ኃላፊነት በመነሣት: ምእመናንና ምእመናት: በፈቃዳቸው የሚያበረክቱትን መባዓቸውን (ስጦታቸውን): ሊያቀርቡ ይችሉ ዘንድ: ሙዳየ ምጽዋቱን: በተለይ በዕለታተ ሰንበትና በዓላት ጊዜ: ከቅዳሴውና ከአንዳንድ ጸሎታት ጋር በማያያዝ: ወንጌል እንደማሳለሙ ሥርዓት እየዞሩ: ለኹሉ እንዲዳረስ የማድረጉ ልማድ ሳይቋረጥ የመቀጠሉ ነገር: ታስቦበት ከተፈጸመ: ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን: አንዱ የገቢ ምንጭ ሊኾን ይችላል::

ለዚህም: ኹለት: የተቆለፉና መኻል ዓናታቸው ላይ: ለገንዘብ ማስገቢያ ያህል: ቀዳዳ ያላቸው: አነስተኛ የእንጨት ሣጥኖች እንዲዘጋጁ በማድረግ: በዚህ ተልእኮ እንዲያገለግሉ የተመደቡ ዲያቆናት ልዑካን: ሣጥኖቹን ይዘው: አንደኛው: በቀኝ፥ ኹለተኛው: በግራ በኩል: ወደእያንዳንዱ ምእመን እየቀረቡ: በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥና ከዚያም ውጪ: በግቢው መዘዋወራቸው: አግባብ ያለው አሠራር ኾኖ ያገለግላል::

ሐ. በልዩ ልዩ መልክ: ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን: ሀብትና ንብረት የኾኑት: የከተማ ቦታዎችና ቤቶች፥ የገጠር መሬቶችና ሌሎች ንብረቶች ኹሉ: እንዳስፈላጊነቱ: በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም: የባለቤትነት ቢጋርና የርስት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲኖራቸው፥ ይህን የመሰለውም ሰነድ: በጥንቃቄ ተጠብቆ እንዲቀመጥ የማድረጉ ኃላፊነት: የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፥ የአስተዳደሩ ጉባኤና የጽሕፈት ቤቱ ሹም መኾኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል::

በዓይነት የሚሰበሰበው ገቢ ኹሉ: በገንዘብ መልክ እየተለወጠ: ለሰበካው አቅራቢያ በኾነው: የታመነ ቤተ ንዋይ ውስጥ: በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም: በሚከፈተው ሒሳብ: ገቢ እየኾነ ይቀመጣል:: በቤተ ንዋይ የሚከፈተው ሒሳብ: ኹለት ዓይነት ቢኾን: መልካም ይኾናል:- ይኸውም:- ፩ኛው: ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ፥ ለሌላም: አስፈላጊ ወጪ: በየጊዜው: የአስተዳዳሪውና የአስተዳደሩ ጉባኤ ምክትል ሊቀመንበር: የጋራ ጽሑፍ ኪዳናት እየሠፈረበት: በመክፈያ ሰነድ የሚንቀሳቀስና ወለድ የሌለው: የአደራ ሒሳብ ሲኾን፥ ፪ኛው: ገንዘቡ: በልዩ ልዩ ሙዓለ ንዋይ ላይ እንዲውል የሚደረግበት: የትርፍ ሒሳብ ነው፤ በዚህ የትርፍ ሒሳብ ውስጥ የሚቀመጠው ገንዘብ: በተቻለ መጠን: ከፍ ያለ ቢኾን: ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን: ከፍተኛ ገቢን የሚያስገኝ ይሆናል::

<u>ስለ፲፪ኛው አንቀጽ:-</u>

ይህ አንቀጽ: በሰበካው ውስጥ ለሚኖሩ: የተመዘገቡ ምእመናን ኹሉ: ለወንዶችም፥ ለሴቶችም: ስለሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ይናገራል::

ምእመናን፡ በበጎ ፈቃዳቸው፡ ለሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ስለሚሰጡት፡ የአሥራት፥ ወይም፡ ሌላ የአስተዋጽዖ ገንዘብ አወሳሰንና አከፋፈል፡ በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከተው፡ ያለምክንያት አይደለም፡፡ ይህ፡ የሰበካ አስተዳደር ደንብ፡ እስከወጣበት ዘመን ድረስ፡ ምእመናን፡ ከቤተ ክርስቲያን፡ በተለይ ለሚሰጣቸው መንፈሳዊ አገልግሎት፡ በጊዜ የተወሰነ መደበኛም ባይኾን፡ የገንዘብ ዋጋ እንዲከፍሉ መደረጉ አልቀረም፡፡

ይኸውም፡ ልጆቻቸውን፡ ክርስትና በሚያስነሡበት ጊዜ፥ ሥርዓተ ተክሊል በሚፈጽሙበት ጊዜ፥ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ፡ ቀዳስያኑ፡ አሉበት ቤት ድረስ ኼደው፡ ቅዱስ ቁርባንን በሚያቀብሏቸው ጊዜና ፍትሓተ ጸሎት በሚካኼድላቸው ጊዜ፥ እነዚህን የመሳሰሉት መንፈሳውያን አገልግሎቶች በሚፈጸሙላቸው ጊዜያት ኹሉ፡ እየተጠየቁ የሚከፍሉት የተወሰነ ገንዘብ ነው፡፡

ምእመናን፡ ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር በእርግጥ የሚገናኙትና የሚቀራረቡት፡ በእነዚህ የአገልግሎት ጊዜያት ብቻ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህም የኾነው፡ ምእመናኑ፡ ለሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው የሚከፍሉት፡ መደበኛ የኾነ ክፍያ ባለመኖሩ ነው፡፡

አኹን ግን፡ በቃለ ዓዋዲ በወጣው፡ በዚህ፡ በሰበካው ጉባኤ አስተዳደር ደንብ መሠረት፡ ይህ ኹሉ ቀርቶ፡ ምእመናኑ፡ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ተመዝግበውና በጠቅላላ ጉባኤያቸው ተስማምተው፡ በፈቃዳቸው፡ የወሰኑትን መደበኛ አስተዋጽዖ፡ በየተወሰነው ጊዜ ስለሚከፍሉ፡ ይህን ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን መፈጸማቸው እየተረጋገጠ፡ ከላይ ለተገለጹት፡ ለክርስትናና ለተክሊል፥ ቅዱስ ቁርባንን፡ በውጭ ለመቀበልና ለፍትሓት እየተባለ፥ መደበኞች ለኾኑት፡ ለመሳሰሉትም መንፈሳውያን አገልግሎቶች፡ አንዳችም ገንዘብ እንዳይከፍሉ ተደርጓል፡፡ ይኹን እንጂ፡ ማናቸውም ምእመን፡ በክርስትናና በተክሊል፥ በሌሎቹም ሥርዓቶች ጊዜ፡ ከደስታም፥ ከመጽናናትም የተነሣ፡ በፈቃዱ፡ በገንዘብም ኾነ፥ በሌላ መልክ፡ ልዩ ስጦታ ላድርግ ቢል፡ አይከለከልም፡፡

"ፍትሓት" የተባለውም፡ በሥጋ ሞት ለተለዩ ምእመናን የሚደረግ፡ የመጀመሪያ የዕረፍት ቀን ጸሎተ ፍትሓት ሲኾን፥ ከዚህ በቀር፡ የሣልስት፥ የሰባት፥ የአሥራ ኹለትና የአርባ ቀን ጸሎተ ፍትሓት እንዲደርስለት የሚፈልግ ምእመን ቢኖር፡ ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጋር ተነጋግሮ፡ ማዘጋጀት ያስፈልገዋል፡፡

እስካኹን፡ በዝርዝር የተገለጸው፡ በጠቅላላ፡ እያንዳንዱን የሰበካ ቤተ ክርስቲያን የሚመለከት ስለኾነ፡ የውጤቱ ጥራትና ትክክለኛነት፥ ወይም፡ ጥፋትና ውድቀት፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪና የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፥ የጽሕፈት ቤቱም ሹም፡ የኀላፊነትና የተግባር ፍሬ፡ የሚገለጽበት፥ የሚታወቅበትና የሚመዘንበት ይኾናል፡፡

<u>ስለ፲፫ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ ስለአውራጃ ሰበካ ጉባኤ አቋም፥ ስብሰባና ተግባር፥ እንዲሁም፡ ስለአባሎቹ ይናገራል፡፡

ከላይ እንደተዘረዘረው፡ በየሥፍራው ተቋቁመው የሚገኙት፡ የሰበካ ጉባኤዎች፡ በአስተዳደር ጉባኤዎቻቸው አማካይነት፡ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው እየተሰበሰቡ የሚሠሩት፡ በየሳምንቱ፥ ወይም፡ እንዳስፈላጊነቱ፡ በየተወሰነ ጊዜ ሲኾን፥ ከእነዚህ፡ በአንድ አውራጃ ግዛት ውስጥ ከሚገኙ፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉባኤዎች ተውጣጥተው የተመረጡት አባሎች ደግሞ፡ በየስድስቱ ወር፡ በአውራጃው ከተማ ውስጥ ይሰበሰባሉ፡፡

የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ፡ ስለሚያስገኘው የሥራ ውጤት፡ ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ፡ ከአውራጃው ሀገረ ስብከት ሊቀ ካህናት በታች፥ ወይም፡ በአውራጃው ሀገረ ስብከት፡ ሊቀ ካህናት የሌለ እንደኾነ፡ ከጠቅላይ ግዛቱ ሊቀ ካህናት በታች፡ በቀጥታ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ነው። ስለዚህ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ፡ የሙያ ችሎታ፥ ንቃትና ትጋት፥ ታማኝነትም ያለው፡ ጠንካራ ሠራተኛ ሊኾን ይገባዋል።

የአውራጃ ሰበካ ጉባኤ፡ በተለይ፡ በቅርቡ፡ በሥራ ላይ ከሚውለው፡ የአውራጃው የውስጥ አስተዳደር ጋር፡ በመተባበር እንዲሠራ ለማድረግ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ፡ ከሌሎቹ ሠራተኞች ጋር፡ ጠንክሮና ተግቶ መሥራት ይኖርበታል።

ከዚህም ጋር፡ በአውራጃው ከሚገኙ፡ ከትምህርትና ከጤና ጥበቃ፥ ከእርሻና ከማኅበራዊ ኑሮ፥ ከሌሎቹም፡ የቤተ ምልክናው መሥሪያ ቤቶች፥ እንዲሁም፡ ከልዩ ልዩ ተመሳሳይ፡ የግልና የሕዝብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር መሥራት ያስፈልጋል።

<u>ስለ፲፩ኛው አንቀጽ፦</u>

ይህ አንቀጽ፡ በጠቅላይ ግዛቱ መንበረ ሊቀ ካህናት ስለሚሰበሰበው የሀገረ ስብከት ጉባኤ የሚዘረዝር ነው።

በአንድ ሀገረ ስብከት፥ ወይም፡ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ባሉ አውራጃዎች የሚገኙ የሰበካ ጉባኤዎች፡ በአውራጃው ግዛት ዋና ከተማ፡ በየስድስቱ ወር የሚሰበሰቡ ሲኾን፡ እነዚህ፡ የአውራጃ ሰበካ ጉባኤዎች ደግሞ፡ በዓመት አንድ ጊዜ፡ በጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ በሚገኘው መንበረ ሊቀ ካህናት ይሰበሰባሉ።

የሀገረ ስብከቱ ጉባኤ ተግባርና የአባሎች ዝርዝር፡ በዚሁ አንቀጽ ተመልክቷል። ይህ ጉባኤ፡ በሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት አማካይነት፡ በጠቅላይ ግዛቱ ደረጃ ካሉት፡ የየምልክናዎቹ ወኪል መሥሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ፡ የግልና የሕዝብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፤ ይኸውም፡ ለአውራጃው እንደተገለጸው ማለት ነው።

የአውራጃ ሰበካ ጉባኤዎችን በመቆጣጠርና በማስተባበር፥ በማነቃቃትም፡ ተፈላጊውን፡ የሥራ ውጤት እንዲያስገኙ የማድረጉ ኃላፊነትና ተጠያቂነት፡ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናት በታች፡ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ስለኾነ፡ ይኸው ሥራ አስኪያጅ፡ ችሎታ፥ ትጋትና ንቃት ያለው፡ ጠንካራና ታማኝ ሠራተኛ መኾን ይኖርበታል።

በተለይ፡ በዚህ አንቀጽ፥ በንዑስ አንቀጽ ፯ (ሀ) የተመለከተው የሀገረ ስብከት ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ አባሎች፡ በቅድሚያ እንዲመረጡና ሥራ እንዲጀምሩ የማድረጉ ኃላፊነት፡ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናትና ሥራ አስኪያጅ ነው። ይህ የሀገረ ስብከት ጉባኤ፡ በቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት እንደሚሰበሰበውና እንደሚሠራው የቤተ ክህነት ጉባኤ ተቋቁሞ በቀዋሚነት የሚሠራ፡ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት የተጣለበት ስለኾነ፡ የአባሎቹ አመራረጥ፡ በጥንቃቄ ሊፈጸም የሚገባ ነው። የሚመረጡት አባሎች፡ የረዥም ጊዜ የሥራ ልምድ፥ በሕዝብም ዘንድ፡ ተደማጭነት ያላቸው፥ በከፍተኛ ቁም ነገር የሚገመቱ መኾን ይኖርባቸዋል። በማናቸውም ጊዜ በሚደረግ ስብሰባ ላይ ለመገኘት እንዲችሉ፡ እዚያው፡ እጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ የሚኖሩ ቢኾኑ ይጠቅማል።

<u>ስለ፲፪ኛው አንቀጽ፦</u>

ይህ አንቀጽ፡ ጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ስለሚሰበሰብበት ጊዜና ቦታ፥ ስለጉባኤውም ዓላማና ተግባር፥ ስለተካፋዮቹም፡ በዝርዝር ያስረዳል።

ይኸው ጠቅላላ ጉባኤ፡ ተገቢው ሥራ እንዲቀርብለት፥ የሚፈለገውንም መልካም ውጤት እንዲያስገኝ፡ ከእጨጌው በታች፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፡ በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት አማካይነት፡ ማናቸውንም ኹሉ ለመፈጸም፡ ግዴታና ኃላፊነት ተጥሎበታል።

እንዲሁም፡ በእጨጌው ሊቀ መንበርነት፡ በከፍተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ደረጃ፡ ስለቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ጉዳዮች፡ የሚሰጠው ውሳኔ ኹሉ፡ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፡ የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ኃላፊነት ነው።

ስለ፲፮ኛው አንቀጽ፡-

ይህ አንቀጽ፡ ስለሰበካዎች አመራርና የአባሎች አበል ይናገራል።

ይኸውም፡-

፩ኛ፡ የሰበካ ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ፥ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ፥ የአውራጃ ሰበካ ጉባኤ፥ የሀገረ ስብከት ጉባኤና የቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ፡ እነዚህ ኹሉ ጉባኤዎች፡ በየደረጃቸው፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት፡ በሚሰበሰቡባቸው ጊዜያት፥

ሀ/ ከጠቅላላ አባሎች መካከል፡ ኹለት ሦስቱ እጅ ከተገኙ፥ ይህም ማለት፡ የአንዱ ጉባኤ አባሎች፡ ለምሳሌ፡ ብዛታቸው፡ ከሊቀ መንበሩ ጋር፡ ሰላሣ ቢኾን፡ ከእነዚህ ውስጥ፡ ሃያው ከተገኙ፡ ጉባኤው፡ እንደሞላ ተቆጥሮ፡ ሥራውን ሊቀጥል ይችላል ማለት ነው።

ለ/ ለየጉባኤው የቀረቡት ጉዳዮች የሚወሰኑት፡ በዕለቱ የተገኙት አባሎች፡ በአንድ ቃል ኾነው ሲስማሙ፥ ወይም፡ በአንድ ቃል ሊስማሙ ያልቻሉ እንደኾነ፡ ለምሳሌ፡- በስብሰባው ላይ የተገኙት፡ ከሊቀ መንበሩ ጋር፡ ሃያ አባሎች እንደኾኑ፥ ከእነዚህ፡ ከሃያዎቹ አባሎች መካከል፡ አሥራ አንዱ፡ በአንድ ወገን ኾነው፡ የተስማሙ እንደኾነ፡ የቀረበው ጉዳይ፡ እንደተወሰነ ይቆጠራል። ነገር ግን፡ የተገኙት አባሎች ቁጥር፡ ከሊቀ መንበሩ ጋር፡ ለምሳሌ፡- ሃያ ቢኾንና በአንድ ጉዳይ ላይ፡ አባሎቹ በሙሉ፡ በአንድ ቃል ባይስማሙና ድምፅ ተሰጥቶ፡ የድምፁ ውጤት ሲቆጠር፡ አሥሩ ደጋፊዎች፥ አሥሩ ደግሞ፡ ተቃዋሚዎች ኾነው ቢገኙ፡ የሊቀ መንበሩ ድምፅ ያለበት ወገን፡ አሥራ አንድ ድምፅ እንዳገኘ ተቆጥሮ፡ ያሸንፋል ማለት ነው።

ሐ/ እነዚህ ጉባኤዎች በሚያደርጉት ስብሰባ ላይ፡ የተወሰኑት ጉዳዮች ኹሉ፡ በቃለ ጉባኤ ተጽፈው፡ ሊቀ መንበሩና የተገኙት አባሎች፡ በሙሉ፡ ጽሑፍ ኪዳናቸውን እንዲያሣርፉበት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም፡ ብዙዎቹ ጉዳዮች፡ በተገኙት አባሎች፡ ሙሉ ድምፅ፡ ተደግፈው የሚወሰኑ ቢኾኑም፡ ምናልባት፡ አንዳንዱ ጉዳይ፡ ደጋፊና ተቃዋሚ ኖሮት፡ በድምፅ ብልጫ ሊወሰን የሚገባ ስለኾነ ነው። በዚህ መልክ፡ የቃለ ጉባኤዎች ጽሑፍ፡ በቅልጥፍናና በጥንቃቄ እንዲዘጋጅ፥ አባሎቹም፡ ቢቻል፡ ወዲያው፥ ባይቻል ግን፡ በማግሥቱ፡ ጽሑፍ ኪዳናቸውን እንዲያሣርፉበት ማድረግ፡ በየደረጃው፡ የጽሕፈት ቤቶች ሹማምንትና ሥራ አስኪያጆች ተግባርና ኃላፊነት መኾኑ፡ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ዘንድ ኹሉ፡ ሊታወቅ ይገባል።

፪ኛ፡ ቀደም ብለው በተዘረዘሩት ጉባኤዎች ላይ፡ ማለትም፡ በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ፥ በአውራጃ ሰበካ ጉባኤ፥ በሀገረ ስብከት ጉባኤና በቤተ ክህነት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ተካፋዮች ለሚኾኑት አባሎች፡ ምናልባት፡ አስፈላጊ ኾኖ የሚከፈል፡ የመጓጓዣና የቀን አበል ቢኖር፡ ይህንኑ ጉዳይ፡ እየራሳቸው ጉባኤዎቹ፡ በየደረጃቸው፡ እንዲወስኑ፡ የአንድ ጊዜ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል።

እንዲህም ቢባል፡ "በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ላይ ለሚገኙት አባሎች፡ የመጓጓዣና የቀን አበል ተመድቦ ይከፈላቸዋል!" ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም፡ እኒህ አባሎች፡ መኖሪያቸው፡ እዚያው በአጥቢያቸው ውስጥ ስለኾነ ነው። ከዚህም ጋር፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት፡ በበለጠ የሚያሳስብና የሚያሳምን፥ በክብደቱም የሚመዝን፡ ከፍተኛ የመሥፈሪያ ነጥብ አለ፤ ይኸውም፡ በማናቸውም ጉባኤ ውስጥ፡ በአባልነት፡ ተሳታፊ የሚኾነው ምእመን፡ አባልነቱ፡ ለኢትዮጵያዊነቱ ሲል፡ በሃይማኖታዊ ቅንዓትና በመንፈሳዊ ፈቃደኛነት፡ ለፈጣሪውና ለወገኖቹ፡ በጎ አገልግሎትን፡ በነፃ ለማበርከት እንጂ፡ ከዚህ ለተለየ፡ ለግል ጥቅም፥ ወይም፡ ለሌላ፡ ባዕድ ዓላማ አለመኾኑን፡ ለራሱም ማረጋገጥ ያለበት መኾኑ ነው። ይህ መሠረታዊ አቋም፡ በማናቸውም ተመራጭ አባል ዘንድ፡ በትክክል የታወቀና ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን ያገኘ መመሪያ መኾን አለበት።

ይኹን እንጂ፡ በመጀመሪያው፡ የአውራጃ ሰበካ ጉባኤ፥ የሀገረ ስብከት ጉባኤና የቤተ ክህነት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ፡ በየደረጃው፡ ከየጉባኤዎቹ እየተወከሉ፡ ወደአውራጃና ጠቅላይ ግዛት ከተሞች፥ እንዲሁም፡ ወደአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ለሚላኩት አባሎች ስለሚያስፈልገው፡ የመጓጓዣና የውሎ አበል የገንዘብ ወጪ፡ የየሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ወስኖ ይመድባል፤ ይህንም ገንዘብ፡ ከሰባካው ምእመናን፡ በሚደረግ ልዩ አስተዋጽዖ፥ ወይም፡ ከበጎ አድራጊዎች ግለሰቦች፥ ማኅበሮችና ድርጅቶች፡ በሚሰጥ እርዳታ፥ ወይም፡ ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ገቢ፡ በሚወጣ ድጎማ፡ መሸፈን ይቻላል።

በየጉባኤዎቹ ስብሰባዎች ላይ ለሚሳተፉት አባሎች፡ ተመድቦ ስለሚከፈለው፡ የመጓጓዣና የውሎ አበል አወሳሰን ጉዳይ፡ በሰበካ አስተዳደር ጉባኤዎች፥ በአውራጃ ሰበካ ጉባኤዎችና በሀገረ ስብከት ጉባኤዎች፡ በየደረጃው፡ ተጠንቶና ተመክሮበት፡ ከተጣራ በኋላ፡ ከየክፍሉ የተገኘው ውጤት፡ ለመጀመሪያው፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ሰበካ ጉባኤ ቀርቦ ሲጸድቅ፡ በተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል።

<u>ስለ፲፪ኛው አንቀጽ፡-</u>

ይህ አንቀጽ፡ የሰበካው አስተዳደር ደንብ፡ በቃለ ዓዋዲው ጦማረ ሕዝብ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ፡ የጸና እንደሚኾን፡ ይናገራል።

ይኸው ደንብ፡ ፍሬያማ እንዲኾን፡ እስካኹን፡ በዝርዝር ሲተነተን በቆየው ማብራሪያ መሠረት፡ ከዚህ የሚከተሉት ቁም ነገሮች፡ ሊታወሱ፥ በሥራ ላይ ውለው፡ እንዲፈጸሙ ማድረግም፡ አግባብና አስፈላጊ ይኾናል።

፩. በዚህ ረገድ፡ ከየጉባኤዎቹ፡ በየደረጃው ስለሚጠበቀው ውጤት፡-

ሀ/ ለሰበካ ጉባኤ፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፥

ለ/ ለአውራጃ ሰበካ ጉባኤ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ፥

ሐ/ ለሀገረ ስብከት ጉባኤ፡ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ፥

መ/ ለቤተ ክህነት ጠቅላላ ጉባኤ፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፡ በቀጥታ ኃላፊዎችና ተጠያቂዎች ናቸው።

፪. በሰበካ ጉባኤ፥ በአውራጃው ሰበካ ጉባኤ፥ በሀገረ ስብከት ጉባኤና በቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፡ ለምክትል ሊቃነ መናብርትነት የሚመረጡት ምእመናን ኹሉ፡ ከተሟላው መንፈሳዊ አቋማቸው ጋር፡ በችሎታቸውና በሙያቸው፥ በሥራ ልምዳቸውና በትጋታቸው፡ የሚበቁ መኾናቸው፥ የመደበኛ ሥራቸው ጠባይም፡ ለሚመረጡበት አገልግሎት፡ የሚረዳ መኾኑ እንዲታይ፥ እንዲታወቅና እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል።

ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ የሚደረገው ምርጫ፡ ትክክለኛ እንዲኾንና ጥንቃቄ እንዳይጎድለው፡ በተለይ፡ በየደረጃው ያሉት የአስተዳደሩ ኃላፊዎች፡ ሊያስቡበትና ሊከታተሉት ይገባቸዋል።

፫. በየደረጃው የሚደረጉትን ጉባኤዎች፡ የመሰብሰቢያቸውን ጊዜያት፡ ከዚህ በሚከተለው መልክ፡ መመደብ ይቻላል፦

ሀ/ የሰበካ ጉባኤን ጠቅላላ ስብሰባ፡ ከነሓሴ ፳፩ እስከጳጉሜ ፩፥ ወይም፡ ፮ ቀን ድረስ ባሉት የቀዳሚትና የእሑድ ዕለታት ሰንበት፥

ለ/ የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ፡ የመጀመሪያ መደበኛ ስብሰባውን፡ በጥቅምት ፲ ቀን ግድም፥ ቢያስፈልግም፡ ኹለተኛውን፡ ከትንሣኤ በኋላ፡ በሚያዝያ ፳ ቀን ግድም፥

ሐ/ የሀገረ ስብከት ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ፡ በጥር ፴ ቀን ግድም፥ ቢያስፈልግም፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ በሚያዝያ ፳፩ ቀን ግድም፥

መ/ የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ጉባኤ፡ በሚያዝያ ወር ማለቂያ፥ ወይም፡ በግንቦት ወር መባቻ ግድም ቢኾን አመቺ ይኾናል።

፬. ይህን፡ የጉባኤዎቹን የመሰብሰቢያ ጊዜያት፡ በደረጃ አመዳደብና አደረጃጀት፥ ከሥራ አፈጻጸሙ ጋር፡ እንዴት ሊካኼድና ሊከናወን እንደሚቻል፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ማብራሪያ፡ በሚበቃ ያስረዳል፦

በመጀመሪያው ደረጃ፡ ከላይ፡ በ፫ (ሀ) የተጠቀሰው፡ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ፡ በጥቅምት ፲ ቀን ግድም ለሚደረገው፡ የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ፡ የሚያቀርበውን፡ የሥራ ፍሬ መግለጫ ለመመርመር፥ በአውራጃው ሰበካ ጉባኤ ላይ ተካፋዮች እንዲኾኑ የሚላኩትን፡ የሰበካ ጉባኤውን ተወካይ አባሎች ለመምረጥ፥ የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን፡ ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል ለመፍቀድና ሌሎቹን፡ በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን ተግባሮች ለመፈጸም፡ በነሓሴ ወርና ከዚያም በፊት፡ ባሉት የወር ቀኖች፡ በየሳምንቱ ቅዳሜ፥ ወይም፡ እሑድ በመሰብሰብ፡ ሥራውን፡ በነሓሴ ፳፩ ቀን ግድም ያጠናቅቃል።

የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ ይህ ተግባሩ እንደተጠናቀቀለት፡ ይህንኑ አቅርቦ ለማስወሰን፥ ወይም፡ ለማስጸደቅ፡ የሰበካው ጠቅላላ ጉባኤ፡ በመስከረም ፲፩ ቀን ግድም ባለው እሑድ እንዲሰበሰብ፡ ጥሪ ያስተላልፋል። በሰበካው ውስጥ የሚኖሩት፡ የተመዘገቡት ካህናትና ምእመናን፡ በዚህ ቀን፡ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ዓፀድ፥ ወይም፡ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው፡ ከሰበካው አስተዳደር ጉባኤ፡ የሚቀርብላቸውን የሥራ ፍሬ መግለጫ ሰምተው፡ ማናቸውንም ጉዳይ፡ በ፩ ድምፅ፥ ወይም፡ ይህ በማይቻልበት ጊዜ፡ በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ።

በሰበካው ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ የተሰጠውን ውሳኔና አስተያየት፡ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ሹም፡ በጽሑፍ አጠናቅቆ፡ በዚያ ቃለ ጉባኤ ላይ፡ ሊቀ መንበሩ፥ ምክትል ሊቀ መንበሩና ሌሎቹ፡ የአስተዳደሩ ጉባኤ አባሎች፥ እርሱ፡ ራሱ ጭምር፡ የየራሳቸውን ጽሑፍ ኪዳን አሥፍረውበት፡ ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል።

በኹለተኛው ደረጃ፡ የአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፡ በአውራጃው ግዛት ውስጥ ከሚገኙት፡ የሰበካ ጉባኤዎች፡ የደረሱትን የሥራ ፍሬ መግለጫዎች አቀነባብሮና የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ የሚነጋገርባቸውን አርእስተ ጉዳዮች አዘጋጅቶ ሲያበቃ፡ በደንቡ ላይ በተመለከተው ሊቀ መንበር ጽሑፍ ኪዳን፡ ከላይ፡ በ፫ (ለ) የተጠቀሰው፡ የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ እንዲሰበሰብ፡ በየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት አማካይነት፡ ለየሰበካ ጉባኤ ሊቃነ መናብርት፡ ማለትም፡ ለየሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፡ ጥሪ ያስተላልፋል።

የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ: በጥቅምት ፲ ቀን ግድም: ስብሰባውን ሊጀምርና ስብሰባውም: እስከሦስት ቀን፥ ወይም: ከዚያ በላይ እንዲቆይ ማራዘም ይቻላል::

የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ: ሥራውን ከፈጸመ በኋላ: የአውራጃው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ: የጉባኤውን የሥራ ውጤት፥ ውሳኔና አስተያየት: በጥንቃቄ አዘጋጅቶ፥ ቃለ ጉባኤውንም: ሊቀ መንበሩና ምክትል ሊቀ መንበሩ፥ እርሱና የአውራጃው ቤተ ክህነት ዋና ጸሓፊ፥ ሌሎቹም: የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ አባሎች: የየራሳቸውን ጽሑፍ ኪዳን አሥፍረውበት: የጉባኤው ስብሰባ በተፈጸመ: ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ: ለሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል::

በሦስተኛው ደረጃ: የሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት: በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ ከሚገኙት: የአውራጃ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤቶች: የደረሱትን የሥራ ፍሬ መግለጫዎች አቀነባብሮና የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ የሚነጋገርባቸውን አርእስተ ጉዳዮች አዘጋጅቶ ሲያበቃ: በደንቡ ላይ በተመለከተው ሊቀ መንበር ጽሑፍ ኪዳን: ከላይ: በ፫ (ሐ) የተጠቀሰው: የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ እንዲሰበሰብ: በየአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት አማካይነትና በቀጥታም: በደንቡ ላይ ለተመለከቱት አባሎች: ጥሪ ያስተላልፋል::

የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ: ጥር ፴ ቀን ግድም: ስብሰባውን ሊጀምር፥ ስብሰባውም: እስከሦስት ቀን፥ ወይም: ከዚያ በላይ እንዲራዘም ማድረግ ይቻላል::

ከላይ: በምሳሌ ቀርቦ እንደተገለጸው: የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ: በጥቅምት ፲ ቀን ግድም ተሰብስቦ፥ የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ ደግሞ: በጥር ፴ ቀን ግድም ቢሰበሰብ የተባለው: ያለምክንያት አይደለም፤ ይኸውም: በኹለቱም ጉባኤዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚላኩት አባሎች: ያው: አንድ ዓይነት ስለኾኑና እነርሱም: በአውራጃው ሰበካ ጉባኤ ላይ ለመገኘት: ከየሰበካቸው: በጥቅምት ወር መጥተው: ስብሰባቸውን እንደጨረሱ: ወዲያው ደግሞ: በሀገረ ስብከቱ ጉባኤ ላይ ለመካፈል: ወደጠቅላይ ግዛቱ ከተማ: ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ: ጥሪ መስጠት፥ ወይም: ባጭር ጊዜ ውስጥ: ወደጠቅላይ ግዛቱ ከተማ: ከየሰበካቸው: እንደገና እንዲመጡ መጥራት: አባሎቹን ማድከምና ማስቸገር ስለሚኾን ነው::

የአውራጃው ሰበካ ጉባኤ: በደንቡ መሠረት: በዓመት: ኹለት ጊዜያት እንዲሰበሰብ ካስፈለገ: አባሎቹ: በቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመገኘት: ወደአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚያደርጉትን ጉዟቸውን ከመጀመራቸው በፊት: ጥቂት ቀኖች: ቀደም ብለው: እግረ መንገዳቸውን: በአውራጃውና በጠቅላይ ግዛቱ ከተሞች በመገኘት: የአውራጃውን ሰበካ ጉባኤያቸውንም ኾነ: የሀገረ ስብከቱን ጉባኤያቸውን አከናነው ማለፍ ይችላሉ::

የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ: ሥራውን ከፈጸመ በኋላ: የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ: የጉባኤውን የሥራ ውጤት፥ ውሳኔና አስተያየት: በጥንቃቄ አዘጋጅቶ፥ ቃለ ጉባኤውንም: ሊቀ መንበሩና ምክትል ሊቀ መንበሩ፥ እርሱና የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሓፊ፥ ሌሎቹም: የሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ አባሎች: የየራሳቸውን ጽሑፍ ኪዳን አሥፍረውበት: የጉባኤው ስብሰባ በተፈጸመ: ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ: ለቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል::

በአራተኛው ደረጃ: የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት: በመላ ኢትዮጵያ ከሚገኙት: የየሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤቶች: የደረሱትን የሥራ ፍሬ መግለጫዎች አቀነባብሮና የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ሰበካ ጉባኤ የሚነጋገርባቸውን አርእስተ ጉዳዮች አዘጋጅቶ ያጠናቅቃል።

አጠናቅቆ እንዳበቃ፡ በደንቡ ላይ በተመለከተው ሊቀ መንበር ጽሑፍ ኪዳን፡ ከላይ፡ በ፫ (መ) የተጠቀሰው፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ሰበካ ጉባኤ እንዲሰበሰብ፡ በየህገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት አማካይነትና በቀጥታም፡ በደንቡ ላይ ለተመለከቱት የጠቅላላው ጉባኤ አባሎች፡ ጥሪ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ሰበካ ጉባኤ የሚሰበሰበው፡ በየዓመቱ፡ በሚያዝያ ወር መጨረሻ፥ ወይም፡ በግንቦት ወር መባቻ ግድም ኾኖ፥ ስብሰባው፡ እስከሦስት ቀን፥ ወይም፡ ከዚያ በላይ እንዲራዘም ማድረግ ይቻላል።

የቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ሰበካ ጉባኤ፡ ሥራውን ከፈጸመ በኋላ፡ የጉባኤው ውሳኔ፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት፡ በተግባር ላይ እንዲውል የማድረጉ ኃላፊነት፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ስለኾነ፡ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ፡ ይህን ኃላፊነቱን ይፈጽማል።

፰. ይህን የሰበካ አስተዳደር ደንብ ለማስፈጸም፡ ከፍተኛውን ኃላፊነትና ተጠያቂነት፥ አደራውንም የተቀበሉት፡ ከእጨጌውና ከየህገረ ስብከቱ ሊቃነ ካህናት፥ ከየጉባኤዎቹ አባሎች ካህናትና ምእመናን ጋር፡ በተለይ፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፥ የየህገረ ስብከቱና የየአውራጃው ሥራ አስኪያጆች፥ እንዲሁም፡ የየሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የጽሕፈት ቤቶቹ ሹማምንት መኾናቸው፡ ሊታወቅ ይገባል። ደግሞም፡ በየደረጃው ባሉት ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙት ሠራተኞች ኹሉ፥ ይልቁንም፡ የሰበካ አስተዳደርን የሚመለከተውን ጉዳይና ተግባር እንዲከታተሉ የሚመደቡት ባለሙያዎች፡ ሥራችን ብለው፡ ይህንኑ ግዳጃቸውን እንዲፈጸሙ ያስፈልጋል።

፱. ይህን ደንብ፡ በሥራ ላይ ለማዋል፡ አግባብነት ያላቸው፡ የጽሕፈትና የምዝገባ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፡ በቅድሚያ መዘጋጀት አለባቸው፤ በተለይ፡ የእያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት፡ የተሟላና የደረጀ ሊኾን ይገባዋል፤ ጽሕፈት ቤቱና መሰብሰቢያው አዳራሹ፡ ወደፊት፡ በጥሩ ዕቅድና ንድፍ ተዘጋጅተው፡ እስኪሠሩ ድረስ፡ በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ፥ ወይም፡ በአካባቢው፡ ለዚህ አገልግሎት ሊውል የሚችል ቤት ካለ፡ ለጊዜው፡ የሰበካውን ጽሕፈት ቤት፡ በዚያ፡ ማቋቋምና ሥራውን መጀመር ይቻላል።

የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን ስም የያዙ፡ ባለአርእስት፡ የጽሕፈት ቤት ማዘዣዎች፥ ማኅተም፥ መታወቂያ ወረቀቶችና ልዩ ልዩ መዛግብት፡ ማለትም፡ መዝገበ ምእመናን፥ መዝገበ ጥምቀት፥ መዝገበ ተክሊል፥ መዝገበ ሙታን፥ እንዲሁም፡ የገንዘብ መቀበያ፥ የገቢ ደረሰኝና የወጪ ማስረጃ፥ እነዚህን የመሰሉ፡ የሒሳብ ማዘጋጃ ዕትሞች ኹሉ መሰናዳት ይኖርባቸዋል።

እነዚህ፡ የሚታተሙ፡ የጽሕፈት፥ የመዝገብና የሒሳብ ወረቀቶች፡ ለእያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ በሚያስፈልገው መጠን፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ተዘጋጅተዋል፤ ወደፊትም፡ ይዘጋጃሉ። ከዚህ መምሪያ ጋር፡ በየዓይነታቸው የተያያዙትን፡ እነዚህን ዕትም ወረቀቶች፡ እያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ ለአውራጃው ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፡ በግልባጭ በማስታወቅ፥ ስላከፋፈሉና ስላላላኩም፡ በቀጥታ፡ ከማተሚያ ቤቱ ጋር በመስማማት፡ በሚያስፈልገው መጠን፡ መጠየቅና መውሰድ ይችላል።

ይህ ማተሚያ ቤት የተቋቋመው፡ ይህን ለመሰለው አገልግሎት መኾኑና ማናቸውም ሥራ፡ ጥሩ ውጤት ሊኖረው የሚችለው፡ በተቀናጀና በተባበረ መልክ ሲካኼድ መኾኑ፡ መቼውንም ይታወቃል።

ስለዚህ፡ ለሰበካ ጉባኤውና ጽሕፈት ቤቱ፥ ለአውራጃው ሰበካ ጉባኤና የቤተ ክህነቱ ጽሕፈት ቤት፥ ለሀገረ ስብከቱ ጉባኤና ጽሕፈት ቤቱ፥ እንዲሁም፡ ለቤተ ክህነቱ ጠቅላላ ጉባኤና ጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ፡ የሚያስፈልጉትን፡ የጽሕፈት፥ የመዝገብና የሒሳብ ዕትሞች፥ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኹሉ፡ ይኸው ማተሚያ ቤት፡ በተሟላ ኹናቴ እያዘጋጀና እያደራጀ እንዲያቀርብ፡ ቋሚ ትእዛዝ የተላለፈለት ስለኾነ፡ ይህ ግዳጅ፡ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚፈጸም መኾኑን፡ የቤተ ክህነቱ ሹማምንት፡ በሙሉ አውቀውት፡ መምሪያው፡ በትክክል፡ በተግባር ላይ መዋሉን፡ በኃላፊነት መከታተል አለባቸው።

የዚሁ ማተሚያ ቤት አድራሻ፡ እንደሚከተለው ነው፡-

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥
መልእክት ሣጥን ቁጥር፡ ፲፪፹፫
ስልክ ቁጥር፡ ፲፩-፶፱-፹፱ እና ፲፩-፸፬-፺፪
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

\+ + +